# ቤዛነት በኃይል

በአክብሮት፡ አመሰግናለሁ። ደህና አመሻችሁ፡ ወዳጆቼ። ዛሬ ምሽት እዚህ መገኘት፡ እንዲሁም በተወደደው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደገና ለእናንተ መናገር ትልቅ መታደል ነው። በማንኛውም ቦታ፡ የእግዚአብሔርን ሕዝብ መገናኘትና፡ ስለዚያ ታላቅ ስም፡ ስለ ኢየሱስ መናገር ሁልጊዜም መታደል ነው።

2 ወንድማችን አሁን የዘመረውን ዝማሬ በእውነት አደንቃለሁ። ያ፡ ያ በጣም የምወደው ነው። ኢየሱስን እንደ ነቢይ ብቻ፡ ወይም እንደ ጥሩ ሰው፡ ወይም እንደ አስተማሪ ብቻ ለማቅረብ በሚሞክሩበት ዘመን፡ ያ ዝማሬ የእርሱን መለኮትነት፡ እርሱ ማን እንደነበረ በግልጽ ያሳያል። እኔም እርሱ እንደዛ እንደሆነ አምናለሁ...

3 በምድር ላይ እንደ እርሱ ያለ አልነበረም፡ አይኖርምም። እርሱ አማኑኤል ነበር። እርሱ አልፋና፡ ኦሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው፥ የነበረው፡ ያለውና፡ የሚመጣው፥ የዳዊት ሥርና ዘር፥ የንጋት ኮከብ ነበር። በእርሱ ውስጥ መለኮት ይኖር ነበር። በእርሱ ውስጥ እግዚአብሔር ነበር።

4 “እግዚአብሔር በልጁ፡ በክርስቶስ ሆኖ፡ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር።” ኢየሱስም፡ “ሥራውን የምሠራው እኔ አይደለሁም፡ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አባቴ ነው። እኔና አባቴ አንድ ነን” አለ፡ እግዚአብሔር በሥጋ፡ ተገለጠ። ለእኛ ያለው የእግዚአብሔር ፍቅር ምንኛ ድንቅ መገለጥ ነው፡ ኃጢአትንና ሕመምን ከሰው ዘር ለማስወገድና፡ ወደ አብ እንደገና ለመቤዠት ሲል፡ ራሱን ዝቅ አድርጎ በሰው ሥጋ ውስጥ አደረ። ያ ድንቅ ነው፡ አይደል? እኛም ያንን በእውነት እናደንቃለን።

5 አሁን፡ ባለፈው ማታ፡ ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ ይመስለኛል። እኔ... ቢሊ፡ ባለፈው ማታ፡ ትንሽ ቶሎ ብሎ ወሰደኝ፡ ምክንያቱም... ደክሞኝ ነበር። ነገር ግን እነዚያ ሰብሰባዎች፡ ያ የመለየት መንፈስ፡ ያ ነገር ምን እንደሆነ ማንም አያውቅም፡ እንደዛ ካልሆነ በስተቀር ብቻ... ያንን ለማወቅ፡ ወደዛ መምጣት አለባችሁ፡ አያችሁ። ለማስረዳት ምንም መንገድ የለም። ማድረግ የ— የምትችሉት መንገድ የለም። ያንን ልምምድ በዚያ ውስጥ የ—የሚያልፉበት ካልሆኑ በስተቀር፡ ማንም አያውቀውም። በሰው ዘር ላይ፡ በአንድ ሰው ላይ የሚያደርገው ነገር፡ ሕይወቱን ከውስጡ ያወጣዋል!

6 እንግዲህ፡ በሁለት ዓለማት ውስጥ ነው የምትሆኑት። **በዚህ** ዓለም ውስጥ ሆናችሁ፡ ደግሞ **በዚያኛው** ዓለም ውስጥ ትሆናላችሁ፡ ከሆነ ሰው ጋር በምትሆኑበት ጊዜ፡ ምናልባት ከአምሳ ዓመት በፊት ከነበረ ሰው፥ ወይም ደግሞ ወደፊት፡ ከዓመታት በኋላ ከሚኖር ሰው ጋር፡ ልትሆኑ ትችላላችሁ፥ ነገር ግን ይህ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ መድረክ ላይ ቆማችሁ፡ ከብዙ፡ ብዙ ዓመታት በፊት የተከሰተ ነገር፥ ምናልባትም ከሳምንታት፡ ወይም ከወራት በፊት፥ በሌላ አገር፡ ወይም በሌላ ሰፍራ፡ የሆነ ነገር እየተናገራችሁ እንደሆነ ትገነዘባላችሁ። ከዚያም በዚህ ሁኔታ ውስጥ ራሳችሁን ቀጥ አድርጋችሁ ለማቆየትና፡ ለማሰብ ትሞክራላችሁ፥ ልንገራችሁ፡ በጣም የሚገርም ነገር ነው። ነገር ግን ጌታ በዚህ

ውስት፡ እስከ አሁን ባለው ሁኔታ ባርኮናል፡ ለዚህም በጣም ደስተኛ ነን፡ አሁንም እግዚአብሔር ከዚህ ስብሰባ ክብር እንደሚያገኝ እናምናለን።

7 አሁን፡ በ—በዛሬ ምሽት አገልግሎት፡ ያሰብኩት፡ አብረን፡ የተሰበሰብነው ጥቂት ሰዎች ብቻ ስለሆንን፥ ስብሰባዎቻችን ማስታወቂያ የተነገረላቸው እዚሁ በአካባቢው ብቻ ነው፡ ለአካባቢው ሰዎች ብቻ ነው የተነገረላቸው። ወደ ሰፊው የስብሰባዎቻችን ክፍል ከመግባታችን በፊት፡ እግዚአብሔር ከላከልን፡ ታላቅ-ነገር፡ በሚመጣበት ጊዜ፡ ያኔ በተሻለ ሁኔታ፡ ሊረዱት እንዲችሉ በማሰብ፥ ምናልባት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ዛሬ፡ የቀድሞውን አይነት ትምህርት ለመስጠት ብሞክር ብዬ አሰብኩ።

8 ከዚህ ሁሉ በኋላ፡ እንደምታውቁት፡ መለኮታዊ ፈውስ ዓሣ ለማጥመድ በመንጠቆው ላይ፡ እንደሚደረግ—ማጥመጃ ብቻ ነው። ያ ብቻ ነው… ዓሣው ማጥመጃውን ይይዝና መንጠቆውንም ይያዛል። ስለዚህ ዋናው… የመጨረሻው ግባችን ይህ ነው፡ ይህም፡ ነፍሳት ለኢየሱስ ክርስቶስ እንዲማረኩ ማድረግ።

9 ዛሬ ምሽት እግዚአብሔር ቢፈውሳችሁ፡ ከመሞታችሁ በፊት እንደገና ልትታመሙ ትችላላችሁ። ከአንድ ዓመት፡ ወይም ከሁለት ዓመት በኋላ፡ እንደገና ልትታመሙ ትችላላችሁ፥ ከአንድ ሳምንት፡ ወይም ከአንድ ቀን በኋላ ልትታመሙ ትችላላችሁ። አላውቅም። ነገር ግን አንድ እርግጠኛ ነገር አለ፡ ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ይህን ዓለም ትታችሁ ትሄዳላችሁ፡ ምክንያቱም ይህ አካላችን ጊዜያዊ ነውና።

10 ነገር ግን ያች ነፍስ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተገናኝታ ዳግመኛ ስትወለድ፡ የዘላለም ሕይወት ይኖራችኋል። እዚህ ምንም ቢፈጠር፡ ፈጽሞ አትጠፋም። ኢየሱስ፡ "ቃሌን የሚሰማ፡ በላከኝም የሚያምን፡ አለው፡" ይህ አሁንን የሚገልጽ ነው፡ "የዘላለም ሕይወት፡ አለው እንጂ፥ ወደ ፍርድ አይመጣም፡" "ነገር ግን ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ፡" ይህ ደግሞ ያለፈ ጊዜ ነው። ያ ሁላችንንም ሜቶዲስቶች አድርጎን በደስታ እንድንጮህ ያደርገናል፡ (አይደል? ) በትክክል፡ እግዚአብሔር ያንን እንዳደረገ፡ ማሰቡ እንደዚያ ያደርገናል። አሁን፡ ያ የእኔ ቃል አይደለም፥ የእርሱ ቃል ነው፡ ዮሐንስ 5፡24።

11 ዮሐንስ 6፡ ኢየሱስ፡ "ሥጋዬን የሚበላ፡ ደሜንም የሚጠጣ፡ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ" አለ። በትክክል። "ሥጋዬን የሚበላ፡ ደሜንም የሚጠጣ፡ ምን አለው፡" አሁናዊ ጊዜ የሚያሳይ ነው፡ "የዘላለም ሕይወት አለው።" አሁን፡ ይህ "ዘላለም፡" ከአንድ መነቃቃት ወደ ሌላው የሚቆይ ብቻ አይደለም፡ ነገር ግን ዘላለምን ሁሉ የሚያልፍ ነው።

12 አሁንም፡ እዚህ ለተቀመጣችሁ ለአንዳንድ አገልጋዮች፡ ያ የዘላለም "ሕይወት" ማለት "የእግዚአብሔር ሕይወት" ማለት ከሆነው ከዚያው ቃል እንደሚመጣ ታውቃላችሁ። ዞዊ የሚለው፡ የግሪክ ቃል፡ "የእግዚአብሔር የራሱ ሕይወት" ማለት ነው።

13 ከዚያም፡ በውስጣችን ባለው በእግዚአብሔር ህይወት አካል፡ የእግዚአብሔር ወንድ ልጅ ወይም ሴት ልጅ፡ የእግዚአብሔር ዘር እንሆናለን። ብንሞክርም እንኳ፡ እግዚአብሔር ሊጠፋ እንደማይችለው ሁሉ እኛም ልንጠፋ አንችልም። ስለዚህ፡ የዘላለም ሕይወት አለን፡ በመጨረሻውም ቀን እንነሳለን።

ያ ድንቅ አይደለምን? ይህ የባፕቲስትና፡ የሜቶዲስት ሰዎችን፡ እርስበርስ እንዲጨባበጡና እንዲጮሁ ያደርጋቸዋል። አይደል? በእርግጥ ያደርጋል። በትክክል።

14 የቀድመው-ዓይነት ሃይማኖት መልካምነቱ ይሄ ነው። ሰዎችን ሁሉ በአንድነት እንዲቀመጡና እርስ በርስ እንዲዋደዱ ያደርጋል። በእርግጥ ያደርጋል። ልዩነቶችን ሁሉ ያስወግዳል፡ አዲስ ፍጥረታት ያደርጋል። ቶክሲዶ የለበሰ—ሰውንና፡ ኦቨርኦል የለበሰን ሰው፡ በአንድነት ተቃቀፈው፡ "ወንድሜ እንዴት ነህ?" እንድባባሉ ያደርጋል፡ በትክክል። በእርግጥ ያደርጋል። የሐር ልብስ የለበሰችንና፡ የጥጥ ልብስ የለበሰችውን፡ ተቃቅፈው "እህቴ፡ እወድሻለሁ" እንዲባባሉ ያደርጋል። የሚያደርገው ያንኑ ነው። በእርግጥ ያደርጋል፡ ልዩነቱን ሁሉ ያፈርሰዋል። "ባለጠጋ ወይም ድሃ፡ ባሪያ ወይም ጨዋ የለም፡ ሁላችንም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ነን።"

15 እሁድ፡ በተርብናክል፡ እዚህ የተቀመጡ በርካታ የታበርናክሉ ሰዎች እንዳሉ አያለሁ፡ "መቤዠት በደም፡" በ—በሚል ርዕስ የ—የሰንበት ትምህርት ተምረን ነበር። እና በሌላ ዓለም ውስጥ ያለሁ እስኪመስለኝ ድረስ፡ **ቤዛነት በደም**፡ በሚለው፡ በዚያ ርዕስ በጣም ተመስጬ ነበር።

16 ዛሬ ምሽት፡ ቤተሰቦቼ ከሄዱ በኋላ፡ እና የመዝሙር አገልግሎቱን ለመስማት እዚህ ቀደም ብዬ ከመጣሁ በኋላ፡ እና ወዘተ፡ ክፍል ውስጥ ነበርኩ። እናም እ... መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ጀመርኩ፡ አንድ ነገርም አገኘሁ። "እንግዲህ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ ዛሬ ምሽት ለጥቂት ጊዜ በዚያ ላይ እናገራለሁ፡" ብዬ አሰብኩ።

17 ስለዚህ፡ እሁድ፡ **ቤዛነት በደም** ነበር። አሁን፡ ዛሬ ማታ፡ **ቤዛነት በኃይል** በሚል ርዕስ እሰብካለሁ። ነገ ማታ ደግሞ (ይህም፡ እግዚአብሔር ቢፈቅድ)፡ **ቤዛነት፡ በሙላት፡ በደስታ** በሚል ርዕስ እሰብካለሁ። ቤዛነት፥ በደም፡ በኃይልና፡ በደስታ!

18 ይህንን ሰበን ለማምጣት... አሁን፡ ብዙ ሰዎች፡ እንደ ጥሩ፡ የተማሩ ሊቃውንት እንዴት አልፈው እንደሚሄዱና የዚህን አይነት መገለጥ፡ ምናልባት፡ **ለዚህ፡** ወይም **ለዚያ፡** ወይም ለአንዳንዱ እንደሚሰጡ ያውቃሉ። እኔ፡ ግን፡ እንደነዚህ ካሉት ካልተማሩ ሰባኪዎች አንዱ ነኝ... የምችለው ብቸኛው ነገር፡ በትክክል ትክክል መሆኔን እርግጠኛ ለመሆን፡ እንዴትም፡ ወደ ጥላዎቹ መሄድ ብቻ ነው። ወደ ግድግዳው መጓዝ ብጀምር፡ እና ብርሃኑ **በዚህ** በኩል ቢሆን፡ እኔ ምን እንደምመስል፡ ልናገር እችላለሁ፥ ባለ አራት-እግር አውሬ፡ ወ—ወይም ወፍ፡ ወይስ ምን እንደሆን፡ የሚያንጸባርቀውን ጥላ ምን አይነት እንደሆነ በማየት ማወቅ እችላለሁ።

19 አሁን፡ ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ነበረ። አሉታዊ ነበር። ልክ እንደ ጨረቃና፡ ፀሐይ፥ ፀሐይ በጨረቃ ላይ ስታበራ፡ ብርሃኑን ወደ ምድር ታንጸባርቃለች። ብሉይ ኪዳንን በጣም እወደዋለሁ! እንደዚህ ባሉ ምሳሌዎች የተሞላ ነው፡ ወይም፡ ልክ እንደዚያ እጅግ የተሞላ ነው። አሁን፡ ፍጹሙ...

20 በዘፍጥረት፡ እግዚአብሔር በመጀመሪያ፡ ፀሐይን፡ ቀጥሎም ጨረቃን በፈጠረ ጊዜ፡ ያቺ ጨረቃና ፀሐይ ክርስቶስንና ቤተ ክርስቲያንን ይወክላሉ። ፀሐይ በኃይሏና በክብሯ እንደምትወጣው ሁሉ፥ ስትጠልቅም፡ ፀሐይ

በሌለችበት ጊዜ ብርሃኗን በምድር ላይ እንድትሰጥ፡ ብርሃኗን በጨለማው ውስጥ ላለችው፡ ጨረቃ ላይ ታንጸባርቃለች። ኢየሱስ፡ በሄደ ጊዜ፡ ወደ ክብር ገባና ብርሃኑን መልሶ በቤተ ክርስቲያን ላይ አንጸባረቀ፥ ይህም እርሱ እስኪመለስ ድረስ የወንጌልን ብርሃንን፡ ለቤተ ክርስቲያን፡ ለመስጠት ነው፡ ኦህ፡ ማይ፡ ከዚያም ይጋባሉ። ያ ድንቅ ይሆናል። ያ አንድ ታላቅ የጨረቃ ብርሃንና... "በጉ የእርሷ ብርሃን ነውና።" በከተማዋ ውስጥ፡ ሌላ ፀሐይ አላስፈለጋቸውም።

21 አሁን ለአጭር ቅድመ ዕይታ፡ ወደ ዘጸአት እንመለስ። በዘጸአት መጽሐፍ ላይ ስናገር እንደማትሰለቹኝ ተስፋ አደርጋለሁ።

22 አንድ ጊዜ፡ ከወንዙ ማዶ ባለው ቤተ ክርስቲያኔ፡ በኢዮብ ላይ፡ ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር ገደማ፡ የሰበክሁ፡ ይመስለኛል። በየምሽቱ ይመጡ ነበር፡ እኔም ከኢዮብ ትንሽ ክፍል እየወሰድኩ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እንዲገጥም እያደረግን፡ እንቀጥል ነበር።

23 እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እርስ በርስ ይገጥማል። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ምንም ዓይነት መጋጨት የለም። የለም፡ ወዳጄ። ሁሉም፡ ፍጹም ነው! በምሪት የተጻፈው ብቸኛው መጽሐፍ፡ ፍጹም በሆነው መልኩ... በብዙ ጸሐፊዎችና፡ በብዙ መቶ ዓመታት ልዩነት ተጽፎ፥ እያንዳንዱ፡ በመንፈስ ቅዱስ ተናጋሪነት፡ እርስ በርሱ በትክክል ይገጣጠማል። ለዚህም ነው፡ እንደ መቃብያንና የመሳሰሉት፡ ተጨማሪ መጻሕፍት፡ ከዚህ ጋር ስለማይገጥሙ፡ የማልቀበላቸው። ለእኔ፡ **ይህ** የእግዚአብሔር ቃል ነው።

24 አንዲት ሴት ደብዳቤ ጽፋ እንዲህ አለችኝ... ያኔ ስለ ኢዮብ በአመድ ላይ ስለመቀመጡ፡ እየሰበክኩ ነበር። እርሷም፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ኢዮብን በአመድ ላይ፡ ለረጅም ጊዜ ያቆየኸው፡ አይመስልህም? ስድስት ሳምንታት ያህል ፈጅተን ነበርና።" "ለመሆኑ፡ ከአመድ ላይ ታስነሳዋለህን፡" አለችኝ?

25 እኔም፡ እንዲህ አልኩ፡ "መንፈስ ቅዱስ ከዚያ ቃሉን መልቀቅ ሲተው፡ ያኔ መናገሬን አቆማለሁ ብዬ እሰባለሁ" አልኳት። መንፈስ ቅዱስ ኢዮብ በአመድ ላይ መሆኑ እንድናገር እስካደረገኝ ድረስ ግን፡ እንግዲህ፡ በዚያው ጾንቼ ቀጠልኩ፥ ነፍሳትም ይድኑ ነበር።

26 ስለዚህ፡ ልክ ወደዚያች ከተማ እንደመጣው፡ እንደዚያ ወንጌላዊ ነው። እርሱ አንድ ምሽት፡ ስለ ንስሐ፡ ሰበከ። በሚቀጥለው ምሽት፡ ስለ ንስሐ ሰበከ። በሚቀጥለው ምሽት፡ እንደገና ስለ ንስሐ ሰበከ። ከአራት ወይም ከአምስት ምሽቶች በኋላ፡ የቤተ ክርስቲያን ቦርድ አባላት አግኝተው እንዲህ አሉት፡ "ወንድም፡ ከንስሐ ውጪ ሌላ ነገር መስብክ አትችልም? "

27 እርሱም፡ "ኦህ፡ እችላለሁ። በመጀመሪያ፡ ሁሉም ንስሐ ይግቡና፡ ከዚያ ሌላ ነገር እሰብካለሁ" አለ። እንግዲህ ያ—ጥሩ ሐሳብ ነው። እነርሱ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ንስሐ ይግባ፡ ከዚያም ሌላ ነገር እንሰብካለን። መልካም።

28 አሁን በተለይ እሑድ ጠዋት በተብርናክል፡ ላልነበሩት ሰዎች፡ ጥቂት ዳራ እናደርጋለን። ወደ ምዕራፍ 12 እንመለሳለን። ነገር ግን የዛሬ ማታ ዋና ሐሳባችን በዘጸአት ምዕራፍ 14፡ ከቁጥር 13 ጀምሮ ይሆናል። እንግዲህ፡ እሁድ ጠዋት፡ "**ቤዛነት በደም፡**" ስንማር ቁጥር 10 ላይ አቁመን ነበር። ታሪኩን ሁላችሁም እንደምታውቁት፡ እርግጠኛ ነኝ።

29 አሁን የዚህን መጽሐፍ ገጾች መግለጥና፡ ማገላበጥ እንደምንችል እናውቃለን። ነገር ግን መጽሐፉን ሊከፍት የሚችል አንድ ብቻ አለ፡ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

30 ዮሐንስ መጽሐፉን አየ። የታተመ ነበር። "በሰማይም ሆነ በምድር፡ ከምድርም በታች መጽሐፉን ሊከፍት የተገባው፡ ማንም ስለሌለ አለቀሰ። ነገር ግን ከዓለም መፈጠር ጀምሮ የታረደ አንድ በግ ነበረ፡ እርሱም መጥቶ በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠው ቀኝ እጅ መጽሐፉን ወሰደ፡ ማኅተሞቹንም ከፈተ መ—መጽሐፉንም ከ—ከፈተ፡ ማኅተሞቹንም ፈታ። ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የታረደ ስለሆነ፡ እርሱ የተገባ ነበር።"

31 እስኪ ዛሬ ምሽት፡ ከእርሱ ጋር እንነጋገር፡ እንዲከፍትልን አሁኑኑ እንጠይቀው።

32 ቸርና፡ አፍቃሪ አባታችን ሆይ፡ አስቀድመን፡ እነሆ፡ በኢየሱስ ስም፡ እየጠራንህ፡ ወደ አንተ እንመጣለን። አሁን ጸሎታችን፡ ይህም፡ ዛሬ ምሽት፡ በውጭ ያ ማዕበል እየተቆጣ፡ በዚህ ጣራ ስር ተጠልለን፡ እዚህ ሰንቆም፡ ዝናቡም እየዘነበና እየነፈሰ ባለበት፡ የምንገባበት የእግዚአብሔር ቤት ስላለን በጣም እናመሰግንሃለን። የመማጸኛ ከተማ፡ መጠለያ ስላለን እናመሰግናለን፥ አንተም፡ "የጌታ ስም የጸና ግንብ ነው፡ ጻድቅም ወደ እርሱ ሮጦ ይድናል" ብለሃልና። የጌታን ስም በማወቃችንና፡ ወደ እርሱ በመምጣታችን እጅግ ደስተኞች ነን።

33 አሁን አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ ይህን ቃል እንድትከፍትልን እንጸልያለን። መንፈስ ቅዱስ መጥቶ በቃሉ ውስጥ ይግባ። የዚህን ምስኪንና ትሑት አገልጋይ ከንፈሮችን፡ እንዲሁም የሚያዳምጡትን የልጆችህን ልቦች፡ ግረዝ። መንፈስ ቅዱስም የእግዚአብሔርን ቃል ወስዶ አስፈላጊ በሆነው ቦታ ሁሉ፡ በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ ያስቀምጠው። አሁን ባርከን። ዛሬ ማታ፡ በመንፈስህ፡ አእምሮአችንን አድስ። ከአገልግሎቱ ክብር ለራስህ ውሰድ። የጠፉትን አድን። የታመሙትን ፈውስ። ያፈገፈጉትን ወደ ቤት መልሳቸው፡ ጌታ ሆይ። እናመሰግንሃለን፡ በተወደደው ልጅህ፡ በኢየሱስ ስም፡ እንጠይቃለንና። አሜን።

34 አሁን ወደ ዘጸአት ምዕራፍ 12 ቁጥር 10 እንመለስ። "**ቤዛነት በደም**" ላይ፡ ስናነብ፡ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ በግ እንዲታረድ እንዴት እንዳዘዘ፡ ምንም ነገር መቅረት እንደሌለበት ስናይ ነበር።

35 ከዚህ በፊት ፍርዶች እየወረዱ ነበር፡ አሁንም የመጨረሻው ፍርድ ሊወርድ ተዘጋጅቶ ነበር። እግዚአብሔር ቃሉን እስከ መጨረሻው ነጥብ ድረስ፡ ሊፈጽም ነበር። እነዚያ ድሮ የነበሩት ፍርዶች ሁሉ፡ አሁን ሊወርዱ ላላቸው ፍርዶች፡ ፍጹም ምልክት ወይም ፍጹም ጥላዎች ነበሩ።

36 ካስተዋላችሁ፡ ፍርዱ ከመውረዱ በፊት፡ አገልጋዮች በዚህ ላይ ከእኔ ጋር ላይስማሙ ይችላሉ፡ ይህም ችግር የለውም፡ ነገር ግን ፍርዱ ግብፅን ከመምታቱ በፊት፡ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ጌሤም ላካቸው። ጌሤም ነበሩ፡ ምንም መቅሰፍትም አልደረሰባቸውም። ይህም በታላቁ መከራ ውስጥ፡ የሚያልፈው የቤተ ክርስቲያን ፍጹም ጥላ ነው፡ አያችሁ። መልካም።

37 ከዚያም ምድርን፡ ወይም ግብፅን የመታው የመጨረሻው መቅሰፍት፡ ሞት ነበረ። እናንተ መጽሐፍ ቅዱስን የምታነቡ፡ የሰንበት ትምህርት

ትምህርቶቻችሁንና የመሳሰሉትን የምታውቁ፡ ይህንን ምናልባት፡ ብዙ ጊዜ፡ ተምራችሁ ይሆናል። ነገር ግን፡ በግብፅ ላይ የደረሰው የመጨረሻው ጠላት ሞት ነበር።

38 አሁን በመንፈሳዊ አነጋገር፡ ቤተ ክርስቲያንን የሚመታው የመጨረሻው ጠላት ሞት ነው። በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ክ—ክርስቶስን የማይከተሉ፡ በመንፈስ ደርቀው ይሞታሉ፥ አብያተ ክርስቲያናትንም፡ አሁን ማየት ትችላላችሁ። ብዙ፡ ብዙ ታላላቅ ሪቫይቫሎችና ወንጌላውያን አገሪቱን፡ ካለፉ በኋላ፡ አሁንም፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ፡ ማለትም፡ ፖለቲካዊ-የቤተክርስቲያን አነጋገር፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየባሰባት ነው። አባላቶቿ የሚፈልጉትን ሁሉ እያደረጉ፡ እንደፈለጉ እየኖሩ፡ ሆኖም ራሳቸውን፡ ክርስቲያን ነን፡ ሁሉም ነገር ደህና ነው ይላሉ።

39 **ክርስቲያን** መሆን ማለት፡ "ክርስቶስን-መምሰል" ማለት ነው። ክርስቶስ በሚመጣ ጊዜ መገኘት በማይገባችሁ ስፍራ አትገኙ። ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ መናገር የማይገባችሁን አትናገሩ። ክርስቶስ በሚመጣ ጊዜ ማድረግ የማይገባችሁ ድርጊት ስታደርጉ አትገኙ። ክርስቶስ በሚመጣ ጊዜ ማሰብ የማይገባችሁ አሳብ አታስቡ። አንድ ዓላማችሁን ጠብቁ፡ ልባችሁም በቀራንዮ ላይ ያተኮረ ይሁን። አሜን። "እርሱ በብርሃን እንዳለ፡ በብርሃንም ብንመላለስ፡ እርስ በእርሳችን ኅብረት አለን፡ የልጁም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም፡ ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።" ያ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ሁላችንንም፡ በአንድነት፡ በእርሱ አንድ ያደርገናል።

40 አሁን፡ የመጨረሻው፡ የመጨረሻው ነገር ሞት ነበር። ያ ሞት ከመምጣቱ በፊት ግን፡ ከሞት ማምለጥ ለሚፈልጉ ሁሉ የሚሆን፡ ማስተሰረያ ተደርጎ ነበር።

41 ከጥፋት ውኃ በፊት ለነበረው ዓለም፡ የመጀመሪያው ጥፋት ከመድረሱ በፊት የማስተሰረያ ተደርጎ ነበር። እግዚአብሔር የጽድቅ ሰባኪ የነበረውን ኖኅን፡ አዘጋጅቶ ነበር፡ እርሱም ሰዎች ወደ መርከቡ እንዲገቡ፡ ለምቶ ሃያ ዓመት ሰበከ። ለመግባት ሆን ብለው እምቢ ያሉት ግን፡ ከፍርድ በቀር የሚጠብቃቸው ምንም ነገር አልነበረም።

42 ዛሬም፡ በክርስቶስ ብርሃን ለመመላለስ፡ እምቢ የሚሉ ሰዎች፡ ምሕረትን ንቃችኋል፡ ስለዚህ ከፍርድ በቀር የሚጠብቃችሁ ምንም ነገር የለም። አለቀ። የምትሄዱባቸው፡ ሁለት አቅጣጫዎች ብቻ ናቸው ያሉት። እናንተም ምርጫችሁን ታደርጋላችሁ።

43 አሁን፡ ያ ታላቅና አ—አስፈሪ ሌሊት ከመምጣቱ በፊት፡ እስራኤል ታዘው እንደነበር፡ እናያለን፡ ያንንም በግ የመታረዱን ጉዳይ፡ አስቀድመን ተመልክተናል።

44 እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያኑን፡ ከግብፅ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለማውጣት፡ ከግብፅ እያወጣት ነበር። ያንን እወደዋለሁ። ምድሪቱን ለመውረስ፡ እየተሻገሩ ነበር። እግዚአብሔር ምድሪቱን ሰጥቷቸው ነበር፡ ነገር ግን በታላላቅ ሕንጻዎችና፡ ቅጥሮች የታጠረች ነበረች። የኢያሪኮ ቅጥርም፡ ሰረገሎች በላዩ ላይ እሽቅድምድም ሊያደርጉበት የሚችሉ ያህል ትልቅ ነበር። ይህን አስቡት፡ ቢሆንም፡ እግዚአብሔር፡ "ለእናንተ ሰጥቻችኋለሁ። የእናንተ ነው" ብሏል። ነገር ግን እነርሱ ማጽዳት፡ አጽድተው ማስወገድ ነበረባቸው።

45 ዛሬም እግዚአብሔር ያደረገው ያንን ነው። የሚፈልግ ሁሉ፡ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት እንዲቀበል፡ ለእያንዳንዳችሁ ሰጥቷችኋል። እናንተ ግን ገብታችሁ፡ መውረስ አለባችሁ፡ አለቀ፥ ልዩነቶችን ተዋግታችሁ አስወግዱ፡ ግንቦቹን አፍርሱ፡ ወደዚያ ገብታችሁ ያንን ያዙ።

46 እናንተም፡ "ፓስተር፡ 'ይህ ለዘመናችን አይደለም' ብሏል" ትሉ ይሆናል። ቀጥ ብላችሁ እለፉት። "እናቴ፡ 'ከቤት አባርርሻለሁ' አለችኝ።" ቀጥ ብላችሁ እለፉት። "ባለቤቴ፡ 'እተውሻለሁ' አለኝ።" ቀጥ ብላችሁ እለፉት። አለቀ። ገብታችሁ መውረስ አለባችሁ! አለቀ።

47 መለኮታዊ ፈውስ ለሁላችሁም ነው። ዛሬ ማታ እዚህ የተቀመጣችሁ፡ ካንሰር፡ የልብ ችግር፡ ወይም ሌላ የፈለገው ይሁን፡ እግዚአብሔር ተስፋውን ሰጥቷል። የእናንተ ነው፡ ነገር ግን ሄዳችሁ መውረስ አለባችሁ።

48 አሁን፡ "እንግዲህ፡ ብዙም ጥሩ ስሜት አይሰማኝም" ትሉ ይሆናል። ከዚያ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ተስፋው የእናንተ ነው። እግዚአብሔር ሰጥቷችኋል። ገብታችሁ ፍልስጤማውያንን፡ ከአንዱ ጫፍ እስከ ሌላው ጫፍ ድረስ ግደሏቸው። ሂዊያንንና አ—አሞራውያንን ሁሉ አውጡ፡ ፈጽሞ አጥፏቸው። ሂዱ፡ ውረሱት። እግዚአብሔር፡ "የእናንተ ነው። ሄዳችሁ ውሰዱት" ብሏል።

49 ነገር ግን እርሱ፡ "አሁን፡ እኔ እሄዳለሁ፡ ሁሉንም አጠፋለሁ፡ ቆንጆ ከተሞችን እገነባላችኋለሁ፡ እንዲሁም ምቾት ላይ አስቀምጣችኋለሁ" አላለም። እንደዚያ አያደርግም።

50 እርሱ ይሰጣችኋል፡ እናንተ ደግሞ ማድረግ ያለባችሁ ነገር አለ። ምድሪቱን ለመስጠት ያህል እሱ ደግ ነው፡ እርሱ እንደሚረዳችሁና ከእናንተ ጋር እንደሚሆን ተናግሯል። ሂዱ፡ ውረሱት!

51 ዛሬ ማታ፡ የታመማችሁ፡ አካለ ስንኩላን፡ ዕውራን፡ ደንቆሮዎች፡ ምንም ብትሆኑ፥ እዚህ ካላችሁ፡ ሂዱና፡ ውረሱ። እግዚአብሔር የእናንተ ነው ብሏል። ርስታችሁ ነው። እግዚአብሔር ሰጥቷችኋል።

52 ያችን ምድር እንደሚሰጣቸው ነግሯቸው ነበር። ወደዚያች ምድር ሊያደርሳቸው፡ መንገዱን እንዲጠብቅ፡ መልአክን በፊታቸው ላከላቸው።

53 እስቲ እንዚያ ሰላዮቹ ወደዚያ በሄዱ ጊዜ ተመልከቷቸው። አሥሩ ተመልሰው መጡና፡ እንዲህ አሉ፡ "ኦህ፡ እኛ አንችላቸውም። የማይቻል ነው። ለምን፡ እኛ ሳይንቲስቶች ነን፡ ነገሩን ሁሉ ተመልክተነዋል። በሳይንስ የማይቻል ነው። ማድረግ አንችልም" አሉ።

54 ነገር ግን ሁለት ሰዎች ነበሩ፡ አንዱ ኢያሱ፡ አንዱ ደግሞ ካሌብ ነበር። ሳይንሳዊውን ጎን ያለውን አይመለከቱም ነበር። የሚመለከቱት እግዚአብሔር ያለውን ነበር። "ማድረግ እንችላለን፡" አሉ። በትክክል። ያች ምድር መልካም እንደሆነች የሚያሳይ ማስረጃ ይዘው መጡ።

55 ለዚያ ማስረጃ እጅግ በጣም ደስተኛ ነኝ፡ (እናንተስ?) ከእኛ በላይ የምትገኝ መልካም ምድር አለችና! እኛም ዛሬ ማታ፡ በጉዞ ላይ ነን። ሃሌ ሉያ! መልካም።

56 አሁን፡ እነሆ፡ ከመቤዠት በፊት ነበሩ። እግዚአብሔር የእስራኤል ልጆች፡ ጥበቃ እንዲደረግላቸው፡ ይህንን በግ እንዲገድሉ አዟቸው ነበር። ደሙንም በመቃኑ ላይ፡ በበሩ አናት ላይና፡ በሁለቱ መቃኖች ላይ፡ **እንደዚህ** እንዲቀቡት ነገራቸው።

57 ገብተውም ይህንን በግ፡ እያንዳንዱን ክፍል መብላት ነበረባቸው፥ አስተውሉ፡ በጉን በሙሉ እንጂ፡ ከፊሉን ብቻ አይደለም። ሁሉም ክፍሉ መበላት ነበረበት።

58 አንዳንዶች፡ "**ይህንን** ክፍል ብቻ እወስዳለሁ፡ **ይህንኛውን** ክ—ክፍል ብቻ አምናለሁ" ይላሉ። ዳሩ ግን ሁሉንም፡ እያንዳንዱን ክፍል መቀበል አለባችሁ። "ኦህ፡ ስለ በደላችን እንደቆሰለ አምናለሁ፡ ነገር ግን፡ 'በቁስሉ' የተፈወስንበትን ክፍል፡ ስለ እርሱ አላውቅም፡" ትላላችሁ። እኛ ግን ሁሉንም እንፈልጋለን። እያንዳንዱ ክፍል መበላት አለበት፥ ሁሉም። አንዳንዱ ክፍል ሊከብድ ይችላል፡ ነገር ግን እንዴትም፡ መብላት አለብን። እግዚአብሔር እንደዚያ ብሏልና።

59 አሁን ቁጥር 10ን አስተውሉ።

> **ከ—ከእርሱም እስከ ጥዋት እንዳች... አታስቀሩ፥ እስከ ጥዋትም...** የቀረውን... **በእሳት አቃጥሉት።**

60 አሁን፡ ምንም ነገር፡ መቅረት የለበትም፥ ሁሉንም። አሁን፡ "ስትበሉት፡ ጥሬ፡ ወይም ያልተብሰለ አትብሉት፡ ነገር ግን በደንብ የተጠበሰ መብላት አለባችሁ፡" አለ። ያ ደስ ይለኛል።

61 ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ለመብላት ሲሞክሩ፡ እንደ ጥሬ ነገር ይወስዱታል፥ ያኘኩታል፡ ይተፉታል፡ ሌላም ነገር ያደርጉበታል። "ኦህ፡ ይህንን መቀበል አልቻልኩም። ልችለው አልቻልኩም፡" ይላሉ። ምክንያቱም በደንብ ስላልበሰለ ነው። ያ ነው በቃ።

62 "በእሳት አብስሉት፡" አለ። እሳት መንፈስ ቅዱስን ይወክላል። በመጀመሪያ እግዚአብሔርን በልባችሁ ውስጥ አስገቡት፡ እርሱም ያበስልላችኋል። በትክክል። በደንብ ይብሰል፡ ይጠናቀቅ፡ በቅመማ ቅመም ይቀመም፡ ያን ጊዜ ጣዕሙ መልካም ይሆናል።

63 አሁን፡ ልክ **እንደዚህ**፡ በውጭ፡ ቆማችሁ፡ "ኦህ፡ ለ—ለእኔ ይሁን፡ አይሁን አላውቅም። ምናልባት ላለፉት ዘመን ይሆናል" ማለት አትችሉም። በመጀመሪያ፡ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉና፡ መለኮታዊ ፈውስ ለእናንተ ምን ማለት እንደሆነ ተመልከቱ።

64 ያን ጊዜ ከልብ-የሆነ ሃይማኖት ለእናንተ ምን ማለት እንደሆነ ተመልከቱ፡ ማለትም ሲመጣ በጉን የሚያበስለውን መንፈስ ቅዱስ ሲኖራችሁ። አሜን። በትክክል። በመጀመሪያ፡ በጉን አብስሉት። ለማብሰያ የሚሆን እሳት ያስፈልጋችኋል። በደንብ መጠበስ አለበት። ኦህ፡ ማይ፡ ያን ጊዜ ነው መልካም የሚሆነው። ጥበሱት፡ ያን ጊዜ ሁሉንም አቃጥሎ...

65 በቅርብ ጊዜ፡ አንድ ትልቅ ብረት ማቅለጫ አጠገብ፡ ቆሜ ነበር፡ እሳቱ ምን ያህል እንደሚሞቅ አስተዋልኩ፡ ዝም ብሎም ይነዳል ይነዳል ይነድ ነበር። በሞቀ ቁጥር፡ በ—በብረቱ ውስጥ፡ በወርቁ ውስጥ ያለው ዝገት፡ ወደ ላይ ይወጣል፡

እነርሱም ያሰወግዱት ነበር። ከዚያም በማቅለጫው ውስጥ እሳቱን ይበልጥ ያቀጣጥሉታል። ከዚያም የበለጠ ሲፈላ፡ ከእርሱ ውስጥ፡ ሌላ ዓይነት ነገር፡ የብረት ማዕድንና የመሳሰሉትን ያወጡለታል።

66 መጀመሪያ የወጣው ቆሻሻ፡ እንደ አፈርና ጭቃ ያለ ነገር ነበር። ቀጥሎ የወጣው እንደ ብረት ያለ ነገር፡ ኦህ፡ ምንም ጥቅም የሌለው ነገር ነበር፥ እንደ ክዊክ ሲልቨር፡ ዝቃጭ የመሳሰሉ ነገሮች ሁሉ፡ ወጡና፡ ተወገዱ። በቀጥታ፡ ወደ ታች ሲወርዱ፡ በመጨረሻ ከውስጡ የወጣው ነገር ፓይራይት ነበር። ይህም የውሸት ወርቅ ነው።

67 ክርስቲያን ሰትሆኑ ወይም ቢያንስ ክርስቲያን እንደሆናችሁ ሰትሆኑ፡ በሰዎች ውስጥ እርስ በርስ ለመታለል የሚሞክሩ፡ ብዙ ነገሮች እንዳሉ፡ ታውቃላችሁ። አያችሁ? ሆኖም መንፈስ ቅዱስ ሁሉንም ነገር እንዲያፈላው ስትፈቅዱለት፡ ከ—ከውስጣችሁ ያሉትን የውሸት ወርቆችንም፡ ጭምር ሁሉ ያወጣላችኋል።

68 የውሸት ወርቅ፡ ብዙ ሰዎች ወደ ምዕራብ ሄደው ያገኟታል፡ ኦህ፡ የወርቅ ማዕድን ያገኙ፡ ይመስላቸዋል። ከእውነተኛው ወርቅ ይልቅ የበለጠ ታብለጨልጫለች። ነገር ግን የውሸት ወርቅ ናት፡ ምንም ዋጋ የላትም።

69 አሁን እነርሱ ያንን ያበሰሉታል፡ ሁሉንም ቆሻሻ ያሰወግዱታል፡ እንዲሁም በውስጡ ምንም ነገር ሳይቀር፡ አንድ መቶ በመቶ ንጹሕ ወርቅ እስኪሆን ድረስ፡ እየቀቀሉ ያበሰሉታል።

70 እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ የሚያደርገውም እንዲህ ነው፡ መንፈስ ቅዱስን ያፈስባታል፡ ዓለማዊነትን፡ ልዩነቶችን፡ ራስ ወዳድነትን፡ ይህንንም ሁሉ አውጥቶ እስኪጥል ድረስ በዚያ ውስጥ ያበሰለዋል፡ ወደ እርሱ በሚመጣው በእያንዳንዱ ግለሰብ ውስጥ አፍልቶ እስኪያወጣው ድረስ። አሜን።

71 አሁን፡ ከዚያ በኋላ፡ መብላት ትችላላችሁ። እዚህ ቁጥር 11 ላይ፡ ሌ—ሌላ ውብ ሐሳብ ይሄውና።

> **ስትበሉ እንደዚህ ትበሉታላችሁ፥ ወገቦቻችሁን** (ይህን አዳምጡ።) **ወገቦቻችሁን ታጥቃችሁ፡...** (ይህ ደስ ይለኛል።)... **ጫማችሁን በእግራችሁ አድርጋችሁ፡... በትራችሁንም በእጃችሁ ይዛችሁ፥ ፈጥናችሁም ትበሉታላችህ፥** እርሱ **የጌታ ፋሲካ ነው።**

72 ይህ ደስ ይላል። ለመሄድ የተዘጋጃችሁ ሆናችሁ፡ ብሉት። ጉዳዩ ይሄ ነው።

73 እስቲ ወደ ኤፌሶን፡ ወደ ኤፌሶን ምዕራፍ 6 እንሂድ፡ ጳውሎስ ቤተ ክርስቲያንን ስለማዘጋጀት ምን እንዳለ እንመልከት፥ 6ኛው ምዕራፍ ኤፌሶን፡ የኤፌሶን 6ኛው ምዕራፍ ከቁጥር 14 ጀምሮ።

> **እንግዲህ፡ ወገባችሁን** በእውነት **ታጥቃችሁ፡... የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥**
>
> **... በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ፥**

**በሁሉም ላይ ጨምራችሁ፡ የሚነበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ፡ ልታጠፉ የምትችሉበትን... የእምነትን ጋሻ አንሡ።**

**የመዳንንም ራስ ቁር፡ የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ፡ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው፡**

74 ጳውሎስ አንድን ሰው ለጦር ሜዳ፡ ለጉዞ ሲያዘጋጀው ተመልከቱ።

75 እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያ፡ እስራኤልን ነጻ ሲያወጣ፡ እንዲህ አለ፡ "አሁን ለጉዞ መዘጋጀት አለባችሁ። በደሙ ስር በሆናችሁ ጊዜ፡ ጫማችሁን አድርጉ። ወገባችሁን ታጠቁ። በትራችሁን በእጃችሁ ይዛችሁ ለጥሪው ተዘጋጁ" አለ። ይህ ደስ ይላል።

76 አንድ ሰው አሁን፡ ወደ ክርስቶስ ሲመጣ፡ ወንጌልን ለመስበክ፡ የወንጌልን ጫማ ያደርጋል፥ የመዳንን ራስ ቁር ይደፋል፥ የጽድቅን ጥሩር ያደርጋል፥ ወገቡንም ይታጠቃል። ይህም...

77 ብዙውን ጊዜ፡ የድሮ ወታደሮች፡ የጦር መሣሪያዎቻቸውን ሲታጠቁ፡ ትልቅ መታጠቂያ ነበራቸው። የጠላት ጦሮች ለመከላከል፡ በወገባቸው ላይ፡ ጋሻቸውን እንዲይዝ አድርገው፡ ይታጠቁት ነበር። ይህ ለእኛ እንዴት ያለ ትልቅ ትምህርት ነው! የ—የወገባቸው መታጠቂያ ሲላላና፡ ሲንጠለጠልባቸው፡ ቀበቶአቸውን፡ በማጥበቅ፡ እንደገና ወደ ቦታው ይመልሱት ነበር።

78 ይህ ዛሬ ምንኛ ፍጹም ምሳሌ ነው! እንደ ላላችሁ ሲሰማችሁ፡ ወይም ዲያብሎስ፡ "ምንም ጥቅም የለውም" ሲላችሁ፡ ወደታች ዘርግታችሁ ቀበቶአችሁን ትንሽ አጥብቁ፥ ሰይፋችሁን በእጃችሁ አጥብቃችሁ ያዙና፡ ወደ ፊት ሂዱ። ይህ ደስ ይላል፡ ለጉዞ ተዘጋጁ።

79 በዚያች ሌሊት፡ በዚያ ደም ሥር ያለፈ ማንኛውም ሰው፡ የጉዞ፡ ትእዛዝ እስኪመጣ ድረስ እንዳይወጣ፡ እዚያው እንዲቆይ ታዞ ነበር።

80 በእግዚአብሔር መንፈስ የተወለደ፡ ወደ ክርስቶስ የሚመጣና፡ የዘላለም ሕይወት ያለው ሰው ሁሉ፥ ጋሻውንና፡ የደረት መታጠቂያውን አድርጎ፡ የጉዞ ትእዛዝ እስኪመጣ ድረስ፡ ሳይለቅ ዝግጁ ሆኖ መቆም አለበት።

81 ኦህ፡ ድንቅ አይደለምን? እናንተ ወታደሮች፡ ዛሬ ማታ ሙሉ ትጥቅ ስለያዛችሁ፡ ደስተኛ አይደላችሁምን?

82 በተብርናክል አንድ የመዝሙር መሪ ነበረን፡ ዋናው መዝሙራችን ይህ ነበር፥

ጦርነቱ ተጀምሯል፡ ኦ ክርስቲያን ወታደሮች፡
በጽኑ እስላለፍ ፊት ለፊት፡
ጦር መሣሪያ ሲያንጸባርቅ፡ ሰንደቅ ዓላማ ሲውለበለብ፡
እውነትና ሐሰት ዛሬ ተፋጠዋል፥
ጦርነቱ ተጀምሯል፡ ነገር ግን አትድከሙ፡
በእርሱ ኃይል ብርቱዎች ሁኑና ጸንታችሁ ያዙ፥
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ፡ ሰንደቅ ዓላማው በእኛ
  ላይ ነው፡
በመጨረሻም የድልን ዝማሬ እንዘምራለን።

83 ብዙዎቹ የቀድሞ ቅዱሳን መካከል ብዙዎቹ ወደ መቃብር ሄደዋል። ነገር ግን ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ በዚያ በአዲሱ ዓለም፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድር በሚወጡበት ጊዜ፡ የመስቀሉ ሰንደቅ ዓላማ በላያችን ይሆናል፡ እኛም የድል መዝሙር እንዘምራለን። በዚያች ሌሊት፡ ለስርግ እራት ስንቀመጥ፡ በደሙ የታጠቡ ቅዱሳን በዚያ ዙሪያ ተቀምጠው፡ ምናልባት መቶ ሺህ ማይል በሚረዝመው፡ በደም-የታጠቡ ቅዱሳን በዚያ ዙሪያ ተቀምጠው። በጠረጴዛው ርዝመት ሁሉ እየተጓዝኩ ከእያንዳንዳቸው ጋር እጅ መጨበጥ እፈልጋለሁ፡ አሜን፡ በደስታ እየጮህኩ። ሰጮኽ መስማት ትፈልጋላችሁ? እዚያ እስክደርስ ድረስ ጠብቁ፥ ጠብቁኝ። ለዚህ፡ ገና፡ አልበቃሁም፣

ነገር ግን፡ አስተውሉ፡ አሁን ጉዞ ላይ ነን። ተዘጋጁ። እየሄድን ነው።

84 ወደ መደበኛ ትምህርታችን ከማለፋችን በፊት፡ እዚህ 38ኛው ቁጥር ላይ የምናገኘው፡ የሚያሳዝን ሁኔታ አለ። አዳምጡ።

ከመንጎቻቸው ጋርና **ሌላም ድብልቅ ሕዝብ** ጋር አብረው ወጡ…

85 እስራኤል የተሳሳቱት እዚያ ላይ ነው። ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገር ተደርጎ ነበር። ያልተለወጠ ሕዝብ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ነገር ስለሆነ ተከተሏቸው፡ በመጨረሻም ችግር ውስጥ አስገቧቸው። ወደ ታች ወረድ ብለን፡ እዚህ በ42ኛውና በ43ኛው ቁጥር አካባቢ፡ እናስተውል። እግዚአብሔር ሙሴን ሲናገረው፡ እንዲህ አለው፡ ይህም፡ "የመሥዋዕት ከሆኑት በቀር… እነሱ መሥዋዕቱን ይብሉ፡" ማለቱ፡ "ነገር ግን ከተገረዙት በስተቀር ማንም እንዳይበላ" አለ። ከተገረዙት በስተቀር እንግዳም ይሁን፡ የውጭ ሰው፡ ወይም ማንም ሊበላው አይገባም።

86 የተወደዳችሁ ወዳጆች ሆይ፡ በዚህ ዘመን፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ፡ የቤተ ክርስቲያን አባል የሆነ ሁሉ፡ የጌታ እራት፡ መውሰዱ ምንኛ ውርደት ነው፡ ይህም ስህተት ነው፡ የተገባቸው፡ የተቤዡት ብቻ ናቸው መውሰድ ያለባቸው።

87 ኢሳይያስ ሲናገር እንዲህ አለ፡ "ማዕዱ ሁሉ ትፋትንና ርኩሰትን ተሞልቶአል።" እንዲህ አለ፡ "ትምህርትን ለማን ያስተምራል? ጡትን ለጣሉ ነውን" አለ። እንዲህ አለ፡ "ትእዛዝ በትእዛዝ፥ ሥርዓት በሥርዓት፥ ጥቂት በዚህ፡ ጥቂት በዚያ ነው" አለ። "መልካም የሆነውን ነገር አጥብቃችሁ ያዙ።" እግዚአብሔር ይህን ሲናገር፡ የምንኖርበት ዘመን፡ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል በፖለቲካ እንደተጠመደችና፡ ሰማቸው በቤተ ክርስቲያን መዝገብ ላይ እስካለ ድረስ፡ ሁሉንም ነገር፡ ሰዎችን፡ እንደምታስገባና፥ ከዚያም አባላት እንደሚሆኑና፡ የጌታ እራት እንደሚወስዱ ስለምያውቅ ነው።

88 መጽሐፍ ቅዱስም፡ "ስለዚህ ሳይገባው፡ ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ፡ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት" ይላል።

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል፡ ምዕራፍ 13 ላይ፡ የተናገረው ይህ ነው።

89 ጳውሎስ፡ ከዓመታት በኋላ፡ በሁለተኛ ቆሮንቶስ ሰዎች ምዕራፍ 11 ላይ፡ እንዲህ አለ፡ ይህም፡ "ስለዚህ ሳይገባው፡ ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ፡ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፡" እንዲህ ይላል፡ "ከመውሰዱ በፊት።" የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እየጠቀስኩ ነው። በትክክል። "ሳይገባው፡ የሚበላና የሚጠጣ፡ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ፡ ለራሱ

ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና። ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ፡ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል።” ከእግዚአብሔር ጋር በትክክል መቆማችሁን እርግጠኞች ሁኑ።

90 ይኸው በጥላው ውስጥ ተመልከቱ፡ ይህም፡ ከተገረዙት በስተቀር ማንም አይውሰድ! ምን ያህል ታማኝ ቢሆን፡ የአይሁድ ቤተ ክርስቲያንን ምን ያህል ቢረዳም ምንም ለውጥ አያመጣም፥ ቅዱስ ቁርባን ከመውሰዱ፡ ወይም የጌታ እራት ከመብላቱ በፊት፡ ወደ አይሁድ እምነት የተቀየረ፡ በእውነት የተገረዘ አማኝ መሆን ነበረበት። ኦህ፡ ዛሬ ከመንገዱ ምን ያህል ነው የወጣነው!

91 አሁን እንደዛ ከሆነ፡ በፍጥነት እንቀጥል። እግዚአብሔር አወጣቸው... አሁን ወደ ዘጸአት ምዕራፍ 14 ቁጥር 13 እንከፍታለን።

92 እግዚአብሔር ከፊታቸው እንድሄድ የእሳት አምድ ሰጣቸው። ዛሬ ማታ፡ እዚህ ምስሉን እንደያዙት አምናለሁ። ይህንን የምናገረው በአክብሮት ነው። በእኔ ታማኝ እምነት፡ ዛሬ ማታ በዚህ ቡድን ውስጥ እያለን፡ ያ የእሳት አምድ ዛሬ ማታ ከእኛ ጋር እንዳለ አምናለሁ። የእስራኤልን ልጆች የመራው ያው የእሳት አምድ፡ በእኛ ፊት እየሄደ፡ ተመሳሳይ ምልክቶችንና ድንቆችን እየፈጸመ ነው። እዚህ ያለ ማንኛውም መምህር፡ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር፡ እስራኤልን የተከተለውና ወደ ተስፋይቱ ምድር የመራቸው መልአክ፡ የቃል ኪዳኑ መልአክ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ያውቃል።

93 ዛሬም፡ ከፈለጋችሁ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለም ያው ነው” የሚለው፡ በእናንተ ዘንድ ሆሊ-ሮለሮች ብላችሁ በምትጠሩት በዚህ ቡድን ፊት እየሄደ ነው። እሺ። ከድል ወደ ድል እየመራ፡ እየቀጠለ ነው! እግዚአብሔር ይመስገን!

94 በዚያ ዘመን፡ በነበሩት አገራት፡ ተንቀው እና ተንቋሽሸው ተጠልተው፡ በአገራት ሁሉ ተገፍተው፡ በብዙ ስም ይጠሩ ነበር።

95 ዛሬም ለእውነተኛው አማኝ፡ ሁኔታው እንደዚያው ነው። ታውቃላችሁ፡ እናንተም፡ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ፡ ለክርስቶስ ስትቆሙና ለእውነት ስትናገሩ፡ መላዋ ቤተ ክርስቲያን፡ “ተመልከቱት! አእምሮውን ስቷል። እብድ ሆኗል” ትላችኋለች። አያችሁ?

96 ለዚያ ትኩረት አትስጡ። ወደ ፊት ቀጥሉ። አሁን ሙሉ በሙሉ ታጥቃችኋል። ደሙም ከፊታችሁ እየሄደ ነው፥ መንፈስ ቅዱስም እየመራችሁ ነው። ዝም ብላችሁ ተንቀሳቀሱ። ማንም የሚላችሁን ነገር አትስሙ። ቀጥታ ወደ ቀራንዮ ተመልከቱና፡ ወደ ፊት ጉዟችሁን ቀጥሉ። ድንቅ ምሳሌ ነው!

97 አሁን፡ ወጥተው ነበር፡ እየሄዱ ሳሉ፡ እናም... አሁንም አስተውሉ፡ የደም ቤዛ ከግብፅ አወጣቸው፡ አሁን ደግሞ ወደ ምድሪቱ የሚያሻግራቸው ሌላ ነገር ያስፈልጋቸው ነበር። አሁን ገና ጉዞ ጀምረዋል። ወጥተዋል፡ ተገርዘዋል፡ በደም ሥር መጥተዋል፡ ጉዞ ላይም ናቸው። አሁን የሆነ ነገር ገጠማቸው። ከሞት ወደ ሕይወት እንዳለፉ እያወቁ፡ የዘላለም ሕይወት እንዳላቸው ገብቷቸው፡ በዚያ ሲሄዱ ነበር።

98 ነገር ግን እነሆ፡ አሁን እየመጡ ሳለ፡ ችግር መነሳሳት ጀመረ። የፈርዖን ሠራዊት፡ ሊይዛቸው፡ እየተከተላቸው መጣ። መከራ ገባ።

99 አዳምጡ! “እግዚአብሔር መጠጊያችንና ኃይላችን ነው፡ ባገኘንም መከራ ረዳታችን ነው።” ኦህ፡ ይህን እንደምታዩት ተሰፋ አደርጋለሁ። አያችሁ? ይኸው ነው። ይህንን በማወቅ... ነገር ግን አዳምጡ፡ አሁን ቁጥር 13፥

**ሙሴም ለሕዝቡ፡ አትፍሩ፡...**

100 ያ ደስ ይላል። ኢየሱስ ከሙታን ከተነሳ በኋላ፡ ቃላቱ ሁልጊዜ፡ “አትፍሩ” የሚል ነበር።

101 ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ችግር ይሄው ነው፡ እንወድቃለን ብላችሁ እስከሞት ትፈራላችሁ። በክርስቶስ ካላችሁ እንዴት ልትወድቁ ትችላላችሁ? ልትወድቁ አትችሉም። የዘላለም ሕይወት አላችሁ። በገሃነም ያሉ አጋንንት ሁሉ ሊያናውጧችሁ አይችሉም። የዘላለም ሕይወት አላችሁ። ኢየሱስ ብሏል። ስለዚህ ስለ ውድቀትን አትፍሩ።

102 “ኧረ፡ እኔ አክራሪ እንዳልሆን እፈራለሁ” ትላላችሁ። ምንም ሳይሠሩ ከመቀመጥ፡ አክራሪነት ብሆን ይሻለኛል። በእርግጥም ይሻለኛል። አንድ ነገር ማድረግ የሚፈልግ ሰው...

103 እዚህ አከባቢ ስለ ባላርድ ይነገራል፡ አንድ ሰው ሥራ ሊጠይቀው መጣና፡ “ስምህን እዚህ ጻፍ፡” አለው። ሰውየው ለመፈረም፡ እርሳሱን አነሳ። “ላጵስህ የት አለ? ” አለው፡

ሰውየውም፡ “እኔ... ምንም ስህተት አልሠራም” አለ።

እርሱም፡ “አንተን መጠቀም አልችልም፡ አንተ ምንም ነገር አትሠራም ማለት ነው” አለው።

104 ልክ ነው። ምንም ዓይነት ስህተት የማትሠሩ ከሆነ፡ ም—ምንም ነገር እየሠራችሁ አይደለም ማለት ነው። እንሂድ፡ ወንድሜ። ተነሱ ጉዞም ጀምሩ። እዚያ ላይ ሎንግፌሎውን እወደዋለሁ፥

ሀዘን ብቻ መሆኗን፡ አትንገረኝ፡
ሕይወት ባዶ ሕልም ብቻ መሆኑን!
ያንቀላፋች ነፍስም ሞታለች፡
ነገሮችም እንደሚመስሉት አይደሉም።

እንዲህ አለ፡

አዎ፡ ሕይወት እውነት ናት! ሕይወት ቅን ናት!
ግቡም መቃብር አይደለም፥
አፈር ነህና፡ ወደ አፈር ትመለሳለህ፡
ይህ ስለ ነፍስ አልተነገረም።

እንነሳና እንስራ፡
ከልብ ለሚመጣው መከራ፥
እንደ አፈ ትብ፡ ከብት አትሁኑ!
ጀግኖች ሁኑ!

105 ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንዲያመጧችሁ አትጠብቁ። እንደ ወንድ ወይም እንደ ሴት ቁሙ፡ እርሱን ተቀበሉት፡ በድልም ወደ ፊት ተራመዱ። አሜን። እግዚአብሔር የሚፈልገው ያንን ነው፡ ብርቱ፡ ዝግጁ የሆኑ ወታደሮችን። መቶ

አምስት ፓውንድ ክብደት፡ ላይኖራችሁ ይችላል፡ ነገር ግን ለእግዚአብሔር መንገዱን ከለቀቃችሁለት፡ ወንድሜ፡ አሁንም በኃይል የተሞላችሁና፡ ብርቱ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ሁለት መቶ ፓውንድ የሚመዝን፡ ነገር ግን አንድ አውንስ እንኳን የወንድነት ባህሪ የሌለው ሰው አይቻለሁ። በትክክል። በጣም ጥሩ። አስተውሉ።

**... ሙሴም ለሕዝቡ፡ አትፍሩ... የእግዚአብሔርን፡ ማዳን እዩ፡...**

106 ያ መልካም ነው። ወደ ፊት ብቻ ተጓዙ። ስለ ምንም ነገር አትፍሩ። ክርስቶስን አዳኛችሁ አድርጋችሁ ከተቀበላችሁ፡ ጉዟችሁን ቀጥሉ።

107 "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትን እፈልጋለሁ።" ጉዟችሁን ብቻ ቀጥሉ። አትፍሩ።

108 "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ አሁን ታምሜአለሁ። ብዙ መሄድ አልችልም፡" ትሉ ይሆናል። አትድከሙ። ጉዟችሁን ብቻ ቀጥሉ፥ የጌታችንን ማዳን ተመልከቱ! ተቀበሉት። ወደ ፊት ብቻ ተጓዙ።

109 "እንዴት ይሆናል? ዶክተሩ ተስፋ ቆርጦብኛል።" አሁን፡ ያ ሰው የተቻለውን ያህል ጥሯል፡ እግዚአብሔር ግን ገና የራሱን የሚችለውን ያህል አላደረገም። በትክክል።

110 ለአንድ አፍታ፡ አሁን እርሱን አዳምጡት። መልካም።

... **ጌታ፡ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን ማዳን እዩ፡ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን** (ፈታኞችን፡ እውነት-... ችግር ፈጣሪዎችን)...

111 እንዲህ ትላላችሁ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ማጨስ ማቆም ብችል! መጠጥ መተው ብችል! መስረቅ ማቆም ብችል ኖሮ! **ይህንን፡ ያንንና፡ ሌላውን** ማድረግ ማቆም ብችል ኖሮ" ትላላችሁ። አትድከሙ። ወደ ፊት ብቻ ተጓዙ። የተቀረውን እግዚአብሔር ይሰራዋል።

112 "ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እንደምችል ባውቅ ኖሮ፡ አሁን በዚሁ ሰዓት ክርስቶስን በተቀበልኩ ነበር።" አትጨነቁ። ቀጥሉበት። ወደ ፊት ብቻ ተጉዙ። የጌታን ማዳን ታያላችሁ!

**... ዛሬ የምታዩአቸውን ግብፃውያንን፡ ለዘላለም አታዩአቸውምና።** (አሜን። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እልባት ያገኛል።)

**እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፡ እናንተም**... **ዝም ትላላችሁ አላቸው።**

**እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፡ ለምን ታለቅቅሰብኛለህ? ወደፊት እንዲጓዙ፡ ለእስራኤል ልጆች ንገራቸው፥** (ይህ ደስ ይላል።)

113 እንዲህ ለማለት፡ አትሞክሩ፡ "አይ፡ ወንድም ብራንሃም፡ እኔ ቤተ ክርስቲያን የተቀላቀልኩት፡ ከዐሥር ዓመት በፊት ነው። ጥሩ ታማኝ አባል ነበርኩ።" ያ ጥሩ ነው፥ አደንቃለሁ። ነገር ግን ዛሬ ማታ፡ ወደ ፊት እንሂድ። እግዚአብሔር

እየተንቀሳቀሰ ነው። ዛሬ እዚህ፡ ያሉ ሰዎች፡ ወደ ኋላ ይመለሱና፡ እንዲህ ይላሉ፡ “ደህና፡ አሁን… ”

114 ሳይንስ፡ ከአንድ መቶ አምሳ ዓመት በፊት፥ በፈረንሳይ አንድ የሳይንስ፡ እንዲህ አለ፡ “አንድ ሰው በሰዓት ሠላሳ ማይል በሚያስፈራ ፍጥነት ቢሄድ፡ የምድር ስበት ከምድር ላይ ይወስደውና፡ ይጠፋል” ብሎ ነበር። ሃህ! በሰዓት ሠላሳ ማይል? አሁንማ በሰዓት ወደ አንድ ሺህ ሰድስት መቶ ማይል እየሄዱ ነው። ያንን ሰው ሳይንስ ተመልሶ ሲጠቅሰው አትሰሙም። በዘመኑ ትክክል ነበር፡ ነገር ግን አሁን ሌላ ዘመን ላይ ነው የሚኖሩት። በትክክል።

115 ነገር ግን፡ እኛ ሰባኪዎችስ፡ ኧረ፡ በፍጹም። “መለኮታዊ ፈውስ? እስቲ አሁን ቅዱስ ሙዲ፡ ፊኒ፡ ኖክስ፡ ካልቪን፡ አንዳንዶቹ ስለ ጉዳዩ ምን—እንዳሉ ልየው።” በዘመናቸው ትክክል ነበሩ። አሁን ግን እየተንቀሳቀሰን ነው፡ ወደ ፊት እየሄድን ነው። ሌላ የተለየ ነገር አግኝተናል።

116 ኢየሱስ፡ በዘሪው፡ ምሳሌ ላይ፡ ዘሪው ወጥቶ ዘር እንደዘራ ተናገረ። እናም የሆነ… ጠላት መጥቶ በሰንዴው መሃል እንክርዳድ ዘራ። “አብረው ይደጉ፡” አለ።

117 ሁል ጊዜ ዓለም ምን ያህል ክፉ እየሆነች እንደሆነ ትጠቁማላችሁ፡ በተመሳሳይ ጊዜ ግን፡ ቤተክርስቲያን ምን ያህል ኃይለኛ እየሆነች እንደመጣች ማየትን ይሳናችኋል። ተነስታ፡ በሜዳው ላይ እየቆመች ነው። ኦህ፡ እርሷ ታናሿ መንጋ ናት፡ ነገር ግን፡ ወንድሜ፡ እግዚአብሔር ከእርሷ ጋር ነው። ክርስቶስ ከሙታን እንደተነሳ ሁሉ እርሷም በእርግጠኝነት ድል ትቀዳጃለች። አሜን። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ፈጽሞ አትወድቅም። “የገሃነም ደጆች አይችሏትም።” እንደሚቃወሟት አሳይቷል፡ ነገር ግን ሊያሸንፏት አይችሉም። ቤተክርስቲያኒቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም፡ በድል ጉዞ፡ ትቀዳጃለች። በአንድ ነገር እርግጠኛ ነኝ፡ እግዚአብሔር ያለ እድፍ፡ ያለ ፊት መጨማደድ፡ ወይም ያለ ነውር የሆነች ቤተ ክርስቲያን ይኖረዋል። አሜን። ስለዚህም በጣም ደስተኛ ነኝ።

118 “አሁን፡ በዚያች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለሁ፡ አሜን! ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ወደ እርሷ የሚገባው እንዴት ነው? በደብዳቤ ነውን? ”

አይደለም።

“ወደ እርሷ እንዴት ትገባለህ? ”

በልደት፡ ወደ እርሷ በመወለድ ነው!

119 በብራንሃም ቤተሰብ ውስጥ ከኖርኩ፡ በሚቀጥለው ሚያዝያ ሰድስተኛ ቀን፡ አርባ-አምስት ዓመቴ ይሆናል፡ ነገር ግን ቤተሰባቸውን እንድቀላቀል ፈጽሞ አልጠየቁኝም። ብራንሃም ሆኜ ነው የተወለድኩት። ሁልጊዜም ብራንሃም እሆናለሁ።

120 በኢየሱስ ክርስቶስ ውስጥ፡ ክርስቲያን ሆኜ ተወለድኩ። ክርስቲያን እሆናለሁ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር በምርጫ፡ እንዲህ እንዲሆን አዟልና። በተወደደው በልጁ ጸጋ፡ ጠርቶናል። እኛም ተቀብለነው የዘላለም ሕይወት አግኝተናል። “በአንድ የእጅ መጨባበጥ”? “በአንድ የአባልነት ምዝገባ”?

“በአንድ የደብዳቤ ማስረጃ”? “በአንድ መንፈስ ሁላችን በአንድ አካል፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ተጠመቅን፡” በዚያም የመንግሥቱ የኅብረት ዜጎች ሆነናል።

121 ዛሬ፡ ጸሎት ላይ ሳለሁ፡ ይህ ዘመን እንዴት ተጠያቂ የምንሆንበት ዘመን እንደሆነ እያሰብኩ ነበር። ከእኔ በፊት ለነበረው፡ ወይም ከእኔ በኋላ ለሚመጣው ትውልድ አልጠየቅም። ነገር ግን፡ በፍርድ ቀን፡ ከዚህ ትውልድ ጋር አብሬ መቆም አለብኝ። እኔም፡ “እዚያ ተመልከቱ፡ ቢራ-የምትጠጣ፡ ሌላም ነገር የምታደርግ፡ የሴት ፎቶ፡ በቢልቦርዱ ላይ ተሰቅሏል፡ ‘ትንፋሽ የለሽ፡’ ወይም የሆነ ነገር ይሏታል።” እኔም፡ “አዎን፡ ህይወት-የለሽ፡ ጭምር ናት” አልኩ። መልካም። ይኸው ነው እያችሁ። እንዲህም አልኩ፡ “እንዴት ያለ ውርዴት ነው!”

122 “ከሰብከቱ ሁሉ ጋር፡” አልኩ፡ “አንዳንድ ጊዜ የሚመስለው፡” ለባለቤቴ ነገርኳት፡ እንዲህ ብዬ፡ “አንዳንድ ጊዜ ምንም ጥቅም የሌለው ይመስላል። ሆኖም ሰዎች ምንም ቢያደርጉም፡ እንዲሁ፡ የማስጠንቀቂያ ድምፅ መሆን አለብኝ። ወንጌልን መናገር፡ እንዲሁ፡ ስለ ትንሣኤና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል መመስከር አለብኝ።” ቢረሱትና፡ ጀርባቸውን ቢሰጡት፡ እግዚአብሔር በፍርድ ቀን ይፈርድባቸዋል። ከእኔ የምጠበቀው ወንጌልን በመስበክ ብቻ ነው፡ ሌሎች ወንጌልን የሚሰብኩ፡ አገልጋዮችም እንዲሁ።

123 አሁን፡ እወደዋለሁ። አስተውሉ፡ “አሁን ወደ ፊት ተራመዱ፡” ያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ክብር ታያላችሁ። ነገር ግን፡ አዳምጡ፡ አሁን ቁጥር 16። ይህንን እናነባለን።

**አንተም... በትርህን አንሣ፡...**

124 “በትር፡” ያ የፍርድ በትር ነበር። አሁን፡ የሙሴ በትር አልነበረም። የእግዚአብሔር በትር ነበር። ካስተዋላችሁ፡ ሙሴ፡ ያንን በትር ወስዶ፡ **እንደዚህ** ወደ ላይ ባነሳው ጊዜ፡ ቅማል መጣ። በውኃው ላይ ባነሳው ጊዜ፡ ወደ ደም ተቀየረ። የእግዚአብሔር የፍርድ በትር ነበር። ያው በትር... ይኸውላችሁ! ያው በትር ነው አለቱን የመታበት፥ ከአለቱም ጎን ሰንጥቅ ተፈጠረ፡ ከእርሱም ውኃ ወጣ።

125 አሁን፡ ያ አለት ክርስቶስ ነበር፡ የእግዚአብሔርም ፍርድ ነበር። “በበላህበት ቀን፡ በእርግጥ ትሞታለህ።” ክርስቶስን በቀራንዮ መታው፡ ያንን መራራና፡ አስቃቂ ሞትም ከፈለ። ማንም ሰው፡ ያ ምን እንደነበር ሊገልጸው አልቻለም፡ ፈጽሞም አይችልምም። እግዚአብሔር ሁሉንም መለኮታዊ ፍርድ በእርሱ ላይ አስቀመጠ፡ ጎኑንም መታው፡ ከጎኑም ለመቤዠታችን፡ ውኃ ደምና መንፈስ ወጣ።

126 ሰዎች አንዳንድ፡ ጊዜ በመስቀል ላይ እንደተሰቀለ፡ በወገቡ የሆነ እንደጠመጠመ፡ ወይም የሆነ ነገር የለበሰ አድርገው፡ ይሥሉታል። ያ ግን እውነት አይደለም። በእርሱ ላይ፡ ሊፈጽሙት የሚችሉትን ማንኛውንም ርኩሰና፡ ዘግናኝ ድርጊት ሁሉ ፈጽመውበታል፥ ነገር ግን ያ መሆን ነበረበት። ይሄውና፡ ከዓለም ሁሉ እጅግ የላቀና ታማኝ የሆነው፡ የነበረና የሚኖር እርሱ ነው። እዚያም በመስቀል ላይ፡ እርቃኑን፡ ቆስሎ፡ ተመትቶ፡ እየደማ፥ የንቀት ምራቅ በፊቱ ላይ ሆኖ፥ በራሱ ላይም የፌዝ የእሾህ አክሊል ተደፍቶ ታየ። ነገር ግን ሞትን፡ ሲኦልን፡ ኃጢአትን፡ ሕመምንና፡ መቃብርን ያሸነፈው፡ ለሁሉላችንም ዋጋችንን የከፈለው ያን ጊዜ ነበር።

127 ብዙ ጊዜ፡ "የሞትን መውጊያ የወሰደው እዚያ ነው፡" ይባላል። ጳውሎስም ያኔ፡ "ሞት ሆይ፡ መውጊያህ የት አለ" ብሏል?

128 ብዙ ነፍሳት፡ እንደ ንቦች ያሉ፡ መውጊያ እንዳላቸውና፡ በዚያም፡ መርዝም እንደሚያስተላልፉ ተነግሮኛል። ነገር ግን አንዴ ከወጉ በኋላ፡ መውጊያቸውን ያጣሉ።

129 ሞት በአንድ ወቅት፡ መውጊያ ነበረው፥ ነገር ግን ክርስቶስ፡ በቀራንዮ፡ የሞትን መውጊያ ነቅሎ ወሰደው። ሃሌ ሉያ! ኦህ፡ ስለዚህ ሳስብ! እዚያ ነበር፡ ለእኔና ለእናንተ፡ የሞትን መውጊያ ሁሉ የነቀለው።ድር

130 ጳውሎስ በሮማውያን እስር ቤት፡ አንገቱ ሊቆረጥ ሲል፡ እንዲህ አለ፡ "ሞት ሆይ፡ መውጊያህ የት አለ?" ወደ ቀራንዮ ጠቆመ፡ የሞት መውጊያ የተነቀለው እዚያ ነበር። "መቃብር ሆይ፡ ድል መንሳትህ የት አለ?" እንዲህ አለ፡ "ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድልን የሚሰጠን፡ እግዚአብሔር ይመስገን" አለ። አሜን። መልካም።

> ... **በትርህን** አንሣ (ፍርዱን)፡ እጅህንም... **በ—በባሕሩ ላይ ዘርጋ፡ ክፈለውም፥ የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ ውስጥ በየብስ ያልፋሉ።**
>
> **እነሆም፡ እኔ፡ የግብፃውያንን ልብ አጸናለሁ፡ በኋላቸውም ይገባሉ፥ በፈርዖንና፡ በሠራዊቱም ሁሉ፡ በሰረገሎቹም በፈረሰኞቹም ላይ፡ ክብር አገኛለሁ።**
>
> **ግብፃውያንም በፈርዖንና በሰረገሎቹ፡ በፈረሰኞቹም ላይ ክብር ባገኘሁ ጊዜ፡ እኔ እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ፡ ያውቃሉ።**
>
> **የእግዚአብሔር መልአክም፡...**

131 አድምጡ! አሁን መታጠቂያችሁን አጥብቁ። "በእስራኤል ሰፈር ፊት ይሄድ የነበረው፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡" አሁንም እዚህ አለ።

> **... በእስራኤልም ሠራዊት ፊት ይሄድ የነበረው፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ ፈቀቅ ብሎ በኋላቸው ሄደ፥ የደመናውም ዓምድ ከፊታቸው ፈቀቅ ብሎ፡ በኋላቸው ቆመ፥** (ወይም፡ **ከዚህ** ተነሰቶ፡ **እዚህ** ከኋላ ቆመ፥ በችግር ጊዜ በመካከል-ቆመ።)

132 ችግር ፊት ለፊት ሲጋፈጣችሁ፡ በየአቅጣጫው በሽታ፡ መከራ ሲኖር፡ የእግዚአብሔር መልአክ ይመጣል፡ በእናንተና በበሽታው መካከል ይቆማል፡ እግዚአብሔር የሰጠውን ቃል እንድትወስዱ ቻለንጅ እያደረጋችሁ፡ በዚያ መንገድ ላይ ይቆማል።

133 እግዚአብሔር ለእስራኤል፡ ወደ ምድሪቱ እንደሚገቡ ተስፋ ሰጥቷቸው ነበር። ምናልባት፡ አንድ ሚሊዮን የሚሆኑ፡ ሰዎች፡ ሊያሳድዷቸው ሊደርሱባቸውና፡ እንደ እንስሳት መንጋ፡ ሊጨፈጭፏቸው፡ እየመጡ ነበር። ነገር ግን እነርሱን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊወስዳቸው፡ እዚያ የነበረው የጌታ መልአክ፡ ከሰፈሩ ተነሰቶ በሕዝቡና በጠላቶቹ መካከል ቆመ።

134 ሃሌ ሉያ! አሁንም ያንኑ ያደርጋል። መንገድ ያዘጋጃል። ኦህ፡ ለዚህም እወደዋለሁ፡ እናንተስ? አሁን እዚህ ለተቀመጠው ለእያንዳንዱ የታመመ ሰው

መንገድ ያዘጋጃል። ቀድሞውንም መንገድ አዘጋጅቷል; በእናንተና በችግሩ መካከልም ቆሞአል።

135 አሁን እዚህ እንዳለ አውቃለሁ። የፈለጋችሁትን አክራሪ ልትሉኝ ትችላላችሁ፥ ለምትናገሩት ነገር ተጠያቂ አይደለሁም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት የምናገረውን፡ ተጠያቂ ነኝ። ነገር ግን በትክክል ከተረዳሁት፡ ዛሬ ምሽት በምታዩት በዚያ ብርሃን ላይ፡ ወይም በዚያ ፎቶግራፍ ላይ ባያችሁት ብርሃን ውስጥ፡ የእስራኤልን ልጆች የመራው ያው መልአክ አለ። ዛሬ ምሽት አውጥተው ያሰቀመጧቸው ይመስለኛል። ያው የእግዚአብሔር መልአክ፡ ኢየሱስ በዚያ ዘመን ያደረገውን ልክ በዚያው መንገድ ለማድረግ፡ አሁን በዚህ ሕንፃ ውስጥ አለ፡ ያን ጊዜ ያደረገውን ለማረጋገጥ እዚህ አለ፡ እርሱ አሁንም ያለ፡ ሁልጊዜም ያው የሆነ ነው። የእግዚአብሔር መልአክ፡ በእኛና በበሽታው መካከል፡ በእኛና በሞቱ መካከል ሊቆም እየመጣ ነው።

136 ዳዊት፡ “በሞት ጥላ ውስጥ እንኳን ብሄድ፡ አንተ ከእኔ ጋር ነህና፥ ክፉን አልፈራም” ማለቱ አያስገርምም። እርግጥ ነው።

137 በዚያ ቆሞ ሳለ፡ በእስራኤል ሰፈር ፊት ይሄድ የነበረው የእግዚአብሔር መልአክ፡ ተነሥቶ ሄደና፡ በእነርሱና በጠላቶቻቸው መካከልም ቆመ።

138 የእግዚአብሔርም መልአክ፡ ዛሬ ማታ፡ እዚህ ባለው እያንዳንዱ ግለሰብና በጠላቱ መካከል ቆሟል። ምን እያወራሁ እንደሆነ አውቃለሁ። ዛሬ ምሽት፡ በዚህ ጥቂት ሕዝብ ፊት፡ እዚህ መድረክ ላይ ቆሜ ሳለሁ፡ እግዚአብሔር ራሱን ዝቅ አድርጎ፡ ከክብር እንደወረደና፡ አሁን በዚህ ሕንፃ ውስጥ እንደቆመ አውቃለሁ። በእግዚአብሔር ቃል ላይ ብቻ ለመንቀሳቀስ ብትደፍሩ፡ በእናንተ ፊት እንዴት እንደሚንቀሳቀስ ታያላችሁ። ተመልከቱ።

139 እርሱም በሰፈሩና በግብፃውያን መካከል መጣ። እርሱ በእናንተና በበሽታችሁ መካከል እየመጣ ነው። አሁንም፡ በእናንተና በኃጢአታችሁ መካከል ቆሟል። ለምን? በቤተ ክርስቲያን መውጣት ጊዜ ላይ ነንና። ግብፅ ሁልጊዜ ዓለም ተብላ ትጠራ ነበር፡ እስራኤል ከግብፅ በወጡ ጊዜ… አስታውሱ፡ በዚያ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን አባላት ነበሩ። ነገር ግን ደሙና ማስተሰረያው ከተደረገ በኋላ፡ በእግዚአብሔር የተገረዙ ሆኑ።

140 እና ዛሬ፡ መገረዝ ማለት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። “ሁላችሁ፡” አለ እስጢፋኖስ፡ “እናንተ ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ ሁላችሁ፡ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ? አባቶቻችሁ እንደሚያደርጉት፡ እናንተም እንዲሁ ታደርጋላችሁ” አለ። መንፈስ ቅዱስ ልብን ይገረዛል፡ የዓለምን ነገሮች ሁሉ ይቆርጣል። የቀድሞ-ዓይነቱ የሆሊነስ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ያ ነበር፡ በዚያ ሁኔታ ይኖሩ ነበር፡ በዚያ ሁኔታ ይንቀሳቀሱ ነበር። ዛሬ፡ ግን፡ ልክ እንደ ቀረው ዓለም ሁሉ ሆኗል። ይህ ውርደት ነው። አጥሮችን አፍርሰናል።

141 ሸማግሌው ወንድም ሰፐርጀን፡ የሜቶዲስት ሰባኪ የሆነው ሸማግሌ ጓደኛዬ እንዲህ ይሉ ነበር፡ አንድ መዝሙርም ይዘምሩ ነበር፡

> አጥሩን አፍርሰናል፡ አጥሩን አፍርሰናል፡
> ከኃጢአት ጋር ተሰማማን።
> አጥሩን አፍርሰናል፡ በጎቹ ወጥተው፡
> ፍየሎች እንዴት ገቡ?

142 ምክንያቱም አጥሩን ስለላፈረሳችሁ! ያ ነው በቃ። የክርስቲያናዊ አኗኗርን መለኪያ አወረዳችሁ፡ ምክንያቱም ሴሚናሪዎች ጥቂት ሰባኪዎችን ፈልፍለው ከእውነት ጋር እንዲያመቻምቹ ልከዋቸዋልና። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ኃጢአትን ለመውቀስ ሁልጊዜ እዚያ ነበር፡ ዛሬ ማታም በአማኙና በዓለም ነገሮች መካከል ቆሟል። አሜን።

**በግብፃውያን ሰፈርና በእስራኤል ሰፈር መካከልም ገባ፥ በዚያም ደመናና ጨለማ ነበረ፡ በዚህ በኩል ግን ሌሊቱን አበራ፥ ሌሊቱንም ሁሉ... እርስ በእርሳቸው አልተቃረቡም።**

143 ተመልከቱ፡ **ለዚህ** አማኞች ቡድን ብርሃን ሆኖ የተሰጠው ያው ነገር፡ ያው ብርሃን፡ **እነርሱን** ያሳውራቸው ነበር።

144 እሺ፡ ድንጋጤን-የሚከላከሉ ጃኬቶቻችሁን ልበሱ። እነሆ እየመጣ ነው። ተመልከቱ፡ ብርሃንን የሚክድ ማንኛውም ሰው ብርሃንን ስላልተቀበለ በጨለማ ውስጥ ይራመዳልና ይታወራል። አሜን። እግዚአብሔር ወንጌልን የሚሰብኩ አገልጋዮችን ይልካል። እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ፡ በመካከላቸው ምልክቶችንና ድንቆችን ይልካል፥ ሰዎች ግን ቢክዱት፡ ከጨለማ በቀር ለእነርሱ የሚቀር ምንም ነገር አይኖርም። ብርሃኑ እያበራ ሳለ በብርሃን ተመላለሱ፡ ወንድሜ። ብርሃኑን ተቀበሉ። ክርስቶስ ብርሃን ነው። ብርሃን ሊያመጣላችሁ መጥቷል። ነገር ግን ብርሃንን የከዱ ጨለማን ተቀበሉ። ዛሬ ማታ፡ ብርሃንን የሚክድ፡ እያንዳንዱ ወንድና ሴት፡ ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ፡ በጨለማ ይራመዳል። በሰዎች ዘንድ ተወዳጅ ሆኖ፡ በጥሩ ሁኔታ እየተጓዘ ነው፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት እንደሚቆም ይገርመኛል።

145 አስተውሉ! እዚህ ምንኛ ድንቅ ነገር አለ! ለአንዱ ብርሃን ነበር፡ ለሌላው ደግሞ ጨለማ ነበር። ከዚያም፡ እስራኤላውያን፡ ሙሴ ከጸለየ በኋላ፡ በሰላም መተኛት ችለው ነበር። አሁን ተመልከቱ።

**ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ፥ እግዚአብሔርም ሌሊቱን ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን አሰወገደው፡ ባሕሩንም አደረቀው፡ ውኃውም ተከፈለ።**

**የእስራኤልም ልጆች በባሕሩ መካከል** በየብስ **ገቡ፡...**

146 አስተውሉ፡ ከጨለማ ወጥተው ብርሃኑን የተቀበሉት፡ የእስራኤል ልጆች፡ ችግር ውስጥ በገቡ ጊዜ፡ ብርሃኑ ተመልሶ መጣ። እነርሱም ሌሊቱን በሙሉ ተኙ። እነርሱ ተኝተው ሳለ፡ እግዚአብሔር በባሕሩ ላይ የሚያልፍ፡ ነፋስ በመላክ፡ የማምለጫ መንገድ እያዘጋጀ ነበር።

147 ለበጉ ሃሌ ሉያ! ዛሬ ማታ፡ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላቴ እጅግ ደስ ብሎኛል። በእግዚአብሔር ተስፋ ላይ እየተኛን፡ እየተደሰትን፡ እያረፍን ሳለ!

148 እግዚአብሔር የማምለጫ መንገድ እንደሚያዘጋጅላቸው፡ ቃል ገብቶላቸው ነበር። እነርሱም በዚህ ተስፋ ላይ እያረፉ ሳለ፡ እግዚአብሔር፡ ከፊታቸው ሆኖ፡ መንገድ እየከፈተ ነበር።

149 ዛሬ ማታ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን በዚህ መሠረት የሚቀበል፡ ማንኛውም ወንድና ሴት፥ እናንተ ተኝታችሁ ሳላችሁ፡ በእርሱ ተስፋ ላይ እያረፋችሁ ሳለ፡ መንፈስ ቅዱስ ይመጣል። ምናልባት አካለ ስንኩል፥ ዕውር፥ ደንቆሮ፥

ማየት የማትችሉ፥ ወይም የታመማችሁ፥ በልብ ህመም፡ በካንሰር፡ በሌላ ነገር ታማችሁ፡ በሞት አፋፍ ላይ ያላችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ዛሬ ማታ፡ ብርሃኑን ተቀበሉና፡ በእርሱ ላይ እረፉ።

150 በጰንጤቆስጤ ቀን እንደመጣው እንደሚነጥቅ፡ ዓውሎ ነፋስ፡ ያ ነፋስ በዚያ በኩል ይወርዳል መንገድም ይከፍትላችኋል፡ ሃሌሉያ፡ በዚያ በበሽታ ሸለቆ ውስጥ በቀጥታ አልፋችሁ፡ እንደገና ወደ ጤና ምድር ትመለሳላችሁ። በዚያ ቀዝቃዛ፡ ወግ አጥባቂ፡ የታሰረና፡ ግድየለሽ በሆኑ ሃይማኖቶች ምድር መካከል በቀጥታ አልፋችሁ፥ በመንፈስ ቅዱስ ወደተሞላ፡ ደስተኛ፡ ሐሴት ወደሚያደርግና፡ በደስታ ወደተሞላ ልብ ትገባላችሁ።

151 እግዚአብሔር ኃይሉን ያሳያል፡ ያሳይም ነበር። ይቅርታ አድርጉልኝ፡ ድምጼን በጣም ከፍ እያደረግሁ ነው። ቤዛነትን በኃይል በማሳየት ላይ። በእርግጥም ደሙን ያኔ፡ በአንድ ነገር ላይ አሳይቷል። በኃይሉ፡ በደሙ በኩል፡ በቤዛነት አማካኝነት አሳይቷል። በደም አማካኝነት፡ ከሞት የማምለጫ ኃይሉን አሳይቷል። በኃይል በመቤዠት የማምለጫ መንገድ፡ የማዘጋጀት ኃይሉን አሳይቷል።

152 እና፡ ዛሬም፡ አሜን፡ ከኃጢአት ሊያነጻችሁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም የተቀበላችሁ፡ እናንተን ወደ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለመምራት የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እዚህ አለ። ከበሽታ ወደ ጤና የሚለውጣችሁ የእግዚአብሔር ኃይል እዚህ አለ። እግዚአብሔር፡ በቤተ ክርስቲያኑ መውጣት ላይ፡ እየተንቀሳቀሰ ነው! እግዚአብሔር፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እህሉን ወደሚሰበስብበት፡ ወደ ማበብ ደረጃ ላይ እየደረሰች ነው። ከጨለማ ወጥቶ፡ ወደ ድንቅ ብርሃን መግባት፡ ምንኛ ድንቅ ነው! ይህንን እንዴት እንወደዋለን! እንዴት እንደምወደው! ዛሬ ማታ፡ ይህ ለነፍሴ ምን ማለት እንደሆነ! ወዳጆቼ፡ እናንተ...

153 ዛሬ ከቤት ውጭ ሳለሁ፡ ካገኘሁት ሰው ጋር ስንነጋገር ነበር። እርሱም፡ "ሰዎችን ለመንገር እየሞከርኩ ነበር" አለኝ። "ቢሊ፡ አንተ ልጅ ከነበርክበት ጊዜ ጀምሮ፡ እኔ በጣም ተቀይሬአለሁ፡" አለኝ። አክሎም፡ "ከዚህ በፊት ወደ ሥራ ቦታዬ እየመጣህ፡ ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ እንዳለብኝ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል መሆን እንዳለብኝ፡ ትነግረኝ ነበር" አለኝ። እንዲህ አለ፡ "እኔም በአንተ ላይ እስቅብህ ነበር። ነገር ግን፡" እንዲህ አለ፡ "ቢሊ፡ አሁን ነገሮች ተቀይረዋል" አለ። "አሁን የምትናገረውን ነገር አውቀዋለሁ፡" አለኝ።

እኔም፡ "እግዚአብሔር ይመስገን" ብዬ አሰብኩ!

154 እርሱም፡ "ለሌሎች ስለ ጉዳዩ ለመናገር እሞክራለሁ፡" እንዲህ አለ፡ "እነርሱ ግን ወዲያውኑ ርዕሱን ቀይረው ስለ አስቂኝ መጽሔት፡ ወይም ስለ ሌላ ነገር ማውራት ይጀምራሉ። 'ኦህ፡ እኔማ አይደለሁም። ጥግ ላይ ያለው ሰውዬ፡ ሊሞት ይችላል፡ ቀጣዩ እሱ ይሆናል። ተራው የእርሱ ነው' ይላሉ፡" ነገር ግን ተራው የማን እንደሆነ አያውቁም። ወዳጄ፡ ዛሬ ማታ፡ ተራው ያንተ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር እናንተን የሚጠራበት ጊዜ ይህ ሊሆን ይችላል።

155 እግዚአብሔር፡ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ፡ ዛሬ ማታ እዚህ፡ በሞትና በሕይወት መካከል፡ በበሽታና በጤና መካከል፡ ቆሟል። ስለ ምን እንደምናገር አውቃለሁ። በትክክል። አሁኑኑ፡ ዳግመኛ-የተወለደ ሰው ሁሉ አሁን የሚሰማችሁን፡ ያንኑ

መንፈስ ቅዱስ በዚህ ክፍል ውስጥ ሳይሰማው አይቀርም። ምንም ማድረግ አትችሉም። የሕይወት እስትንፋስ ካላችሁ፡ እርሱ እዚያ እንዳለ ታውቃላችሁ። መልካም።

156 እንደ ማግኔት ነው፡ ልክ… አንድ ትልቅ ማግኔት ወደ ቁሳቁስ ሲቃረብ፡ እየተቃረበ ሲመጣ፡ (ለምን? ) መንቀሳቀስና መሳሳብ ይጀምራሉ። በአንድ ወቅት፡ በሃሞንድ፡ ኢንዲያና፡ አንድ ትልቅ ማግኔት ወደ ታች እንደወረደው ነው። መሬት ላይ ያሉትን ፍቅፋቂዎች ሲያነሳ፡ እየተመለከትኩ ነበር። አንድ ትልቅ መቆጣጠሪያ ጎተቱ፥ አንድ ትልቅ ማግኔት ወደ ታች ወረደ። ፍቅፋቂዎቹን ሁሉ ጠርገው በመሬቱ መካከል አድርገዋቸው ነበር። በአጠገቡ ሲያልፍም፡ ወደ ማግኔቱ የተሳቡት እነዚያ ፍቅፋቂዎች በሙሉ፡ ብረቶቹ፡ በቀጥታ ወደ ላይ ወጡና ከማግኔቱ ጋር አብረው፡ ወጡ። ከዚያም ማግኔትነቱን ሲያቆሙት፡ ወደ ማቅለጫው ውስጥ ጣሉትና፡ እንደገና ቀረጹት። ብዙ የአሉሚኒየም ቁርጥራጦች ግን ቀርተው ነበር። እኔም "እነዚህ ለምን አልሄዱም? " አልኩ፡

እርሱም፡ "ለማግኔቱ ማግኔጢሳዊ ስላልሆኑ ነው" አለኝ።

157 እኔም፡ "እግዚአብሔር ይመስገን" አልኩ። "እዚህ ጋር፡ ይሄ የብረት ቁራጭስ፡ ለምን አልሄደም፡" አልኩ?

እርሱም፡ "ካስተዋልከው፡ በብሎን ታስሮ ነው ያለው" አለኝ።

158 ወዳጆች ሆይ፡ ዛሬ ምሽት ይህ የብዙ ሰዎችን ሁኔታ ይመስላል። የቤተ ክርስቲያን አባል ሆናችኋል፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ማግኔጢሳዊ አልሆናችሁም። ከዚያም የሆነ ነገር፡ የሆነ ልዩነት፡ አስሮ እንዲይዛችሁ ትፈቅዳላችሁ።

159 ነገር ግን ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው፡ ታላቁ ማግኔት ከምሥራቅ ይመጣል፡ ይህችንም ምድር ይጠርጋታል። በክርስቶስ የሞቱትም ሁሉ ወደ ማዶ ለመሄድ፡ ከእርሱ ጋር ይነሳሉ። እነዚህም ያረጁ አካላት የክብሩንም አካል እንዲመስሉ፡ በእርሱ አምሳል ይለወጣሉ፡ በዚያም ከበሽታ፡ ከእርጅናና፡ ከማንኛውም ነገር ነጻ ሆነን፡ በእግዚአብሔር ክብር ውስጥ፡ በዚያ በተባረከው መገኘቱ፡ ለዘመናት እንኖራለን። አሜን። ይህ እንዳያስደነግጣችሁ። አሁን መንፈስ ቅዱስ እየተሰማኝ ነው። አዎን። መልካም።

160 "ቤዛዬ ሕያው እንደሆነ፡ በመጨረሻው ቀንም በምድር ላይ እንደሚቆም አውቃለሁና፥ ምንም እንኳ ትሎች ይህን አካሌን ቢያጠፉትም፡ በሥጋዬ ግን እግዚአብሔርን አያለሁ፥ እኔ ራሴ አየዋለሁ፥ ሌላ ሳይሆን፡ ዓይኖቼ ይመለከቱታል።"

161 ያበድኩ አይምሰላችሁ። አይደለሁም። ብሆንም እንኳ፡ ዝም በሉኝ። ከሌላው ይልቅ እንደዚህ ሲሆን በጣም ደስተኛ ነኝ። አዎ፡ ጌታዬ። እንደዚሁ ልቆይ። ኦህ፡ እርግጥ ነው፡ ለዓለም፡ "እብድ" ነኝ፡ ምክንያቱም፡ ዓለም እብድ የሚላቸውን ነገሮች፡ እግዚአብሔር የተባረኩ ይላቸዋል። ለዚህ ዓለም፡ "አእምሮአችሁን ማጣት" አለባችሁ፡ ምክንያቱም (ለምን? ) እናንተ የዚህ ዓለም አይደላችሁም።

162 ያንን የመለያ መስመር ስትሻገሩ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ትሆናላችሁ። ኦህ፡ ማይ! ምን ያህል ድንቅ ነው? ለምን፡ ከዚህ አሁን ካላችሁበት

ሁኔታ ተለውጣችሁ፡ (ኦህ፡ ማይ) አዲስ ፍጥረት ትሆናላችሁ። "አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። አሁን በሰማያዊ ሰፍራ አብረን ተቀምጠናል።" በሺህ ዓመት ግዛት ውስጥ፡ "እንሆናለን፡" አይደለም። አሁን ነን፡ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን። "አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ፡ በሰማያዊ ሰፍራ አብረን ተቀምጠናል፡" በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን፡ "በክርስቶስ ኢየሱስ።"

163 ከሙታን የተነሳው ጌታ ኢየሱስ እዚህ አለ። እርሱ በኃይሉ እዚህ አለ። እርሱ በሚቤዥ ኃይሉ እዚህ አለ። እርሱ ለዘጸአት እዚህ አለ። እያንዳንዱን የቤተ ክርስቲያን አባል ከእርሱ ጋር ወደ ኅብረት ለማምጣት እዚህ አለ። እያንዳንዱን ኃጢአተኛ፡ ምንም ያህል ዝቅ ብትል፡ የትንሣኤውን ኃይል ወደ ሕይወትህ ለማምጣትና አዲስ ፍጥረት ለማድረግ እርሱ እዚህ አለ።

164 ከጥቂት ዓመታት በፊት፡ እዚህ፡ የዓለም ሃይማኖቶች ሁሉ ተገናኝተው ነበር፡ በለንደን፡ እንግሊዝ፡ ወይም የሆነ ቦታ ይመስለኛል። በትክክል አላስታውሰም። ነገር ግን፡ ሁሉም ስለተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት፡ መሐመዳውያን፡ ቡድሃዎችና፡ ሁሉም ሲናገሩ፡ አንድ ምስኪን... የአሜሪካን ሆሊነስ ቤተ ክርስቲያንን የወከለ አንድ ሰው፡ ጆን ዊት፡ መሰለኝ፡ ሰሙ፡ ስለዚህም እርሱ፡ የመናገሪያ ተራው ደርሶ ሲነሳ፡ በዚህ ታላቅ ሰብሰባ ላይ ለተወከሉት ሃይማኖቶች ሁሉ፡ ስለ ሌዲ መቃቢ ታሪክ ነገራቸው፡ እሷ ምን ያህል እርባና ቢስ እንደነበረች፥ በኦክላሆማ በቁጥጥር ስር ውላ፡ ሲጋራ በአፏ ይዛ፡ እየነዳች... ወይም የፍጥነት ወሰን ጥሳ፡ በሠረገላ በጎዳናዎች ሰትጋልብ እንደነበረ ተናገረ። በጣም ብዙ ግድያዎችን የፈጸመች፡ በጣም ርኩሰና፡ እጅግ ክፉ ከመሆኗ፡ የተነሳ፡ ሊቀጧትና ሊያዋርዷት ሲመጡ፡ እንዳንረክስ ብለው፡ እጃቸውን እንኳ ሊጭኑባት አልፈለጉም ነበር።

165 ታሪኩን በጣም በሚመሰጥ ሁኔታ ተናግሮ ሲጨርስ፡ እያንዳንዱ አድማጭ በመቀመጫው ጫፍ ላይ ተገትሮ ነበር። እንዲህ አለ፡ "እናንተ የዚህ ዓለም ሃይማኖቶች፡ መሪዎች ሆይ፡ የእናንተ ሃይማኖት የሌዲ መቃቢን እጆች ሊያነጻ የሚችል የሆነ ነገር አለውን? " ማንም አንዲት ቃል አልተናገረም። እርሱም ወደ ላይ ዘሎ ተረከዞቹን አጋጨና፡ እጆቹን አጨበጨበ። እንዲህም አለ፡ "የኢየሱስ ክርስቶስ ደም እጇቿን ብቻ ሳይሆን፡ ልቧንም ያነጻል።" አሜን። በትክክል።

166 የኢየሱስ ክርስቶስ ደም በሉዊስቪል፡ ኬንታኪ ያለችውን እጅግ እርባና ቢስ የሆነች አመንዝራ ወስዶ፡ ጨዋ ሴትና፡ ቅድስት ያደርጋታል። በዚያ ማዶ ያለውን የሕገ ወጥ መጠጥ አዘዋዋሪውን ወስዶ፡ ጨዋ ሰውና፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ ያደርገዋል።

167 ወዳጆቼ፡ የመንግሥቱ ዜጎች፡ የኬንታኪና የኢንዲያና፡ እንዲሁም በአካባቢው ያላችሁ ወገኖቼ ሆይ፡ የመጨረሻው ዕድላችሁ ከማለፉ በፊት፡ ዛሬ ምሽት፡ ስለዚህ ስለ ጌታ ኢየሱስ የምታሰቡበት ጊዜ አሁን አይመስላችሁምን?

168 ቤተ ክርስቲያን በዚህ ታላቅ ዘጸአት ውስጥ ስትሄድ ስታዩ፡ የእሳቱ ዓምድ በፊታችን እየመራ፡ ቆሞ፡ ተአምራትንና ምልክቶችን ሲያደርግ ስታዩ፡ እርሱ ዛሬ ምሽት፡ በሚቤዥ ኃይሉ ሁሉ፡ እዚህ አለ፥ እያንዳንዱን ኃጢአተኛ፡ ሙሉ ለማድረግ፡ እያንዳንዱን ወደኋላ ያፈገፈገውን ለመመለስ፡ እያንዳንዱንም የታመመ ሰው ለመፈወስ እዚህ አለ።

169 እርሱ ሙሉ ወንጌል ነው። እኛም ሙሉውን ወንጌል እንሰብካለን፥ በጉንም በሙሉ እንበላለን። በመንፈስ ቅዱስ ጠበሱት፡ ሙብላቱም መልካም እንደሆነ እወቁ፡ ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ እርሱ በጣም ጥሩ እንደሆነ ገልጦልናልና። “እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ፡ ቅመሱ እዩም። እንደ ዓለት ማር ይጣፍጣል።”

170 ጌታችን ኢየሱስ በፍቅሩና በኃይሉ፡ በታላቅ የመቤዠት በረከቶቹ፡ እዚህ አለ! ኦህ፡ ዛሬ ምሽት በቤተ ክርስቲያንና፡ በኃጢአት መካከል እንዴት ይቆማል! ደም እየፈሰሰ፡ እየጸለየ፥ በአንተና በፍርድ መካከል እንዴት ይቆማል!

171 በቅርብ ጊዜ፡ እዚህ ኦሃዮ ውስጥ ወደሚገኝ አንድ ቦታ ገባሁ፡ በዚያም የራሴን ስለ ፍርድ ያለኝ አመለካከት ልሰጥ ተቃርቤ ነበር። በአንድ ትንሽ የደንካርድ ምግብ ቤት እመገብ ነበር። ትልቅ ሰብሰባ እያደረግን ነበር። ከከተማው ጥቂት ማይሎች ርቆ በሚገኝ፡ አንድ ትንሽ ሞቴል ውስጥ መቆየት ነበረብኝ። በዚያ የደንካርድ ምግብ ቤት እመገብ ነበር፥ በጣም ደግና ጥሩ ሰዎች ነበሩ፡ እሑድ ዕለት ግን ዘግተው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዱ ነበር። እኔም ምሳዬን ለመብላት፡ ወደ አንድ የተለመደ፡ ትንሽ የአሜሪካ ምግብ ቤት መሄድ ነበረብኝ።

172 በሩን ከፍቼ ስገባ፡ የሚገርም ነገር አጋጠመኝ፡ አንድ የክልል ፖሊስ አንዲት ሴት አቅፎ፡ ቁማር መጫወቻ ሲጫወት ቆሟል። ቁማር በኦሃዮ ሕገወጥ ነው፡ እዚያ ግን ሕግ አስከባሪው ራሱ ሕግ ሲጥስ ይታያል። ምናልባትም፡ በእኔ ዕድሜ ያለ ያ ሰው፡ የሆነ ቦታ ላይ፡ ሚስትና ቤተሰብ ያለው ሳይሆን አይቀርም፥ እዚያ ግን አንዲትን ወጣት አቅፎ ቆሟል።

173 ምግብ ቤቱን መለስ ብዬ ሰመለከት፡ አንዳንድ ወጣቶች፡ እዚያ ኋላ ሰክረው፡ ተቀምጠዋል፡ አንዲት ወጣትም በፍጹም ከሥነ ምግባር ውጭ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ነበረች።

174 እኔም ተመለከትኩ፡ ቁጭ ብዬ፡ በሰተቀኝ በኩል፡ ወደ አንድ ክፍል፡ ልቀመጥ በተዘጋጀሁበት፡ እዚያ፡ አንዲት በእድሜ የገፋች ሴት ተቀምጣለች፡ ዕድሜዋ አምሳ-ሰምንት፡ ሰልሳ ዓመት ገደማ የሚሆን፡ እንደ እናቴ ያረጀች፥ ቆዳዋ ሁሉ የተጨማደደ፡ አጭር ልብስ ለብሳ፡ እዚያ ተቀምጣለች። እናም፡ አቤት፡ በጣም የሚሰቀጥጥ ነበር። የእግር ጥፍሯ ሐምራዊ ቀለም የተቀቡ፡ ከንፈሯም ሐምራዊ የተቀባ ነበር፡ አይታችሁት የማታውቁት እጅግ አሰቀያሚ-እይታ ነበር። ፀጉሯ በጣም አጭር ተቆርጦ **እንደዚህ** ተንጨባርሯል። ትጠጣም ነበር።

175 ሁለት ወንዶች ከእርሷ ጋር፡ ተቀምጠው ነበር፡ መልካቸው-የሚያስፈራና፡ የሰከሩ ነበሩ፡ አንደኛውም በጠረጴዛው ላይ ባሉት ሳህኖች ላይ ተደፍቶ ነበር። ይቅርታ መጣሁ በማለት ለመውጣት፡ ወደ መጸዳጃ ቤት ሲወጡ…

176 እዚያ ቆሜ ነበር። እንዲህም ብዬ አሰብኩ፡ “ኦ አምላክ ሆይ፡ ይህንን እንዴት ትታገሣለህ? እንዲህ ያለውንስ ነገር እንዴት ታያለህ? ምንም እንኳ እኔ ራሴ፡ በልቤ፡ ደካማ ብሆንም እንኳ፡ አሁንም፡ ትንንሾቹ ሳራና ርብቃ እንዲህ ባለ ትውልድ ውስጥ ማደጋቸውና እንዲህ ያለውን ነገር ማየታቸው አይቀሬ ነው ብዬ አሰባለሁ። ጌታ ሆይ፡ ይህን ነገር ከምድር ገጽ ላይ ለምን ፈጽመህ አታጠፋውም? ” “ጌታ ሆይ፡ ለምን አታደርገውም? ” ብዬ አሰብኩ።

177 እዚያው ተቀምጬ ማልቀስ ጀመርኩ። ራእይም አየሁ። ያየሁትም፡ ዓለም በአየር ላይ ስትሽከረከር፡ አየሁ፡ በዓለም ዙሪያ ቀስተ ደመና ቆሞ ነበር። የሚያናግረኝም ሰው፡ እንዲህ አለኝ፡ “ይህ በዓለም ዙሪያ ያለ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው፡ ዓለምን እንዳያጠፋት የሚከለክለው እርሱ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአትን ካየ፡ ‘ከዚያ በበላህ ቀን፡ ሞትን ትሞታለህ’ እንደተባለው ነው። በዚያ ደም ስር ያለ እያንዳንዱ ሰው እንኳ፡ የ... የራሱን ምርጫ እንዲያደርግ፡ ነጻ የፈቃድ ምርጫ ተሰጥቶታል። ነገር ግን ብትሞቱና፡ ነፍሳችሁ የዚያን ደም ምሕረት አልፋው ብትሄድ፡ እዚያ ከመድረሳችሁ በፊት ቀድመውኑ ተፈርዶባችኋል። የቀረላችሁ ምንም ነገር የለም” አለኝ።

178 ከዚያም ራሴን አየሁ። የእሾህ አክሊል በራሱ ላይ ደፍቶ፡ ጌታዬ ኢየሱስ ቆሞ አየሁት፡ እናም ደም የተቀላቀለ እንባ፡ ጺሙን አልፎ ሲፈስ፡ እዚያ ቆሞ አየሁት። ኃጢአቶቼም በፊቱ ሲቀርቡ አየሁ፡ በእያንዳንዱ ጊዜም በፊቱ እንዲህ በቀረቡ ቁጥር፡ [በቴፕ ላይ ያለ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።]... ይንቀጠቀጥ ነበር። እሾሁም በግንባሩ ላይ፡ ይበልጥ ይገባ ነበር። እርሱም ወደ ኋላ ይንገዳገድ ነበር። “አባት ሆይ፡ የሚያደርገውን አያውቅምና፡ ይቅር በለው፡” ይል ነበር። እኔም እንደገና የሆነ ነገር አደርጋለሁ፡ ያኔ ደሙ መክና እንደሚከላከል፡ እንደ መኪናን መከላከያ ሆኖ፡ ካልተገባኝ፡ ከእግዚአብሔር ቁጣ ይጋርደኝ ነበር።

179 ቀስ እያልኩ፡ ወደ እርሱ ቀረብኩ፡ በፊቱም ተንበረከክሁ። እንዲህ አልኩ... በፊቴ ወድቆ ወደነበረው፡ መጽሐፍ ተመለከትኩ፡ የቆየ የኃጢአት መጽሐፍ ነበረ፡ በላዩ ላይም ስሜ ተጽፎ ነበር። “ጌታ ሆይ፡ ይቅር ትለኛለህን፡” አልኩት?

180 በፍቅር ዓይኖቹ እያየኝ፡ “በእርግጠኝነት፡” አለኝ፥ ወደ ጎኑ እጁን ሰደደ፡ ደም አውጥቶም፡ “ይቅር ተብሏል፡” ብሎ ጻፈበት። የመረሳት ባሕርም ውስጥ ወረወረው። እንዲህም አለኝ፡ “አሁን... ”

እኔም፡ “ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ” አልኩት።

181 እርሱም እንዲህ አለኝ፡ “አሁን፡ እኔ ይቅር ብዬሃለሁ፥ አንተ ግን ትፈርጃታለህ።” ኦህ፡ ይህ ለእኔ፡ ምስሉን ለወጠው።

182 ከ—ከዚያም ከራእዩ ወጣሁ። ወደ እሷም ሄጄ አጠገቧ ተቀመጥኩና፡ ማውራት ጀመርኩ። እናም እሷ በፊት አስቸጋሪ ህይወት አልፋለች። “ክርስቲያን አልነበርሽም፡” ብዬ ጠየቅኳት?

እሷም፡ “ያደግሁት በክርስቲያን ቤት ነው” አለችኝ።

እኔም፡ “ታዲያ ምን ተፈጠረ” አልኳት?

183 ከባሏ ጋር ስለነበራቸው አለመግባባት፡ ስለ ልጆቿና፡ ስለመሳሰሉት ነገሮች ነገረችኝ። እኔም፡ “በነዚህ ዓመታት፡ ሁሉ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ከተገናኘሽበት ጊዜ ጀምሮ በፍጹም ሰላም ኖረሽ አታውቂም ወይ” አልኳት?

እሷም፡ “ጌታዬ፡ እውነቱ ያ ነው” አለችኝ።

እኔም፡ “ታዲያ አሁን አትቀበዪውም” አልኳት?

እሷም፡ “ይቀበለኛል ወይ” አለችኝ?

እኔም፡ “አሁን በልብሽ ደጃፍ እያንኳኳ ነው” አልኳት።

184 ከዚያም ከመቀመጫዋ ተነስታ፡ እዚያው ወለል ላይ፡ በዚያ ሁሉ ሕዝብ ፊት ተንበረከከች፥ የቁማር መሣሪያዎቹ ቆሙ፡ የብልግና ሰድቦች ቆሙ፡ ሁሉም ነገር ጸጥ አለ። እጆቹንም ወደ ላይ አነሳሁ፡ እጆቹንም... እነዚያንም ምስኪን የተሸበሸቡ እጆቿን ይዤ፡ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መራኋት። በትክክል። ይኸው ነው፡ ወዳጆች ሆይ። ሌላ አትጠብቁ... ኢየሱስ...

185 ምንም ያደረግኸው ቢኖር፡ ኃጢአትህ ምንም ያህል የጠቆረ ቢሆን፡ ሕይወትህ ምንም ያህል የቆሸሸ ቢሆን ግድ የለኝም፥ እግዚአብሔር፡ ዛሬ ምሽት፡ ማንንም ብትሆን፡ አንተን ይቅር ለማለት በልብህ ደጃፍ ቆሞ፡ እያንኳኳ ነው።

186 ለጥቂት ጊዜ ራሳችንን ዝቅ እናድርግ። እህቴ፡ ወደ ኦርጋኑ ነይልን፡ እባክሽ?

187 የሰማይ አባት ሆይ፡ ኦህ፡ መንፈስ ቅዱስ አሁን በዚህ ሕንፃ ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ባለበት በዚህ ሰዓት... እጸልያለሁ። በመጀመሪያ የአንተን ሞገስ ለማግኘት፡ መንግሥትህን እንድንፈልግ እርዳን፡ ከዚያም የታመሙትን እንደምትፈውስ አምናለሁ። ነገር ግን አሁን፡ አባት ሆይ፡ ታላቅና፡ ጥልቅ የሆነ ፍላጎትና ልብን የሚነካ እምነት እየተሰማን፡ ቤተ ክርስቲያንህ በዘጸአት ላይ እንዳለችና፡ ወደ ፍርድ እየሄድን እንደሆነ ሰዎች ያውቃሉ። ሳናውቅ ግን፡ ነገ ጠዋት፡ የሆነ ሰው ወደ አልጋችን መጥቶ፡ እኛን በሕይወት አያገኘን ይሆናል፡ ሄደን ሊሆን ይችላል። ነገ ምሽት፡ በዚህ ሰዓት፡ የሆነ የሬሳ ክፍል ውስጥ ልንገኝ እንችላለን፡ ነፍሳችንም በዚያ በዘላለም ዓለም ትሆን ይሆናል።

188 አምላክ ሆይ፡ ይህ ምናልባት የመጨረሻው ሰዓት ሊሆን ይችላል! ይህ ሰው የሚያገኘው የመጨረሻው ዕድል ሊሆን ይችላል። እዚህ ከተቀመጡት፡ ብዙዎች፡ ያለጥርጥር፡ ወንዶችና ሴቶች፡ ፍላጎት ያላቸው፡ መልካም ሕይወት የኖሩ ቢሆንም፡ ዳግመኛ ግን ያልተወለዱ እንዳሉ፡ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፡ ሙሉ በሙሉ የተሰጠ ሕይወት ማለት ምን እንደሆነ የማያውቁ፥ ሰንሰለቶችና፡ ሕፍረት ሁሉ፡ ተወግዶላቸው፡ የእግዚአብሔር መንፈስ በምሕረቱ ውስጥ እንዲያጠምቃቸው የሚያስፈልጋቸው አሉ።

189 ውድ፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ ምሽት፡ በተወደደው ልጅህ፡ በኢየሱስ ስም፡ በእያንዳንዱ ልብ ውስጥ፡ ተንቀሳቅሰህ አሁን አትናገርምን? እነርሱም፡ በልባቸው ቅንነት፡ ሃሳባቸውን ወደ አንተ ቢያነሱና፡ ልባቸውን ከፍ አድርገው እንዲህ ቢሉ፡ "ኢየሱስ ሆይ፡ እነሆ መጥቻለሁ። አሁን እንዳለሁኝ፡ ውሰደኝ፡ ቅረጸኝና ሌላ የተለየ ነገር አድርገኝ። እንድሆን የምትፈልገው ዓይነት ሰው አድርገኝ። በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፡ ተናግረኸኛል። እናግረኸኛል። የተለየ ነገር እንዳደርግ ሞክረሃል። ራሴን እንድሰጥህ ለማድረግ ሞክረሃል። አሁን ግን ጌታ ሆይ፡ ቀኑ መሽቶብኛል፡ እኔ ግን አሁን ለመምጣት፡ ዝግጁ ነኝ።" አድርግልን፡ አባት ሆይ። ምሕረት እየጠራ ባለበት በዚህ ሰዓት፡ ከፍርዱ በፊት፥ የቤተ ክርስቲያን መውጣት ጊዜ፡ ከግብፅ እየወጣች ባለበት ጊዜ፥ እነርሱም መጥተው፡ ተጠርጠው-ከወጡት፡ ከዚህ ታላቅ ቡድን ጋር አብረው ይሂዱ። በስሙ እንለምናለን።

190 አሁን ራሳችንን ዝቅ አድርገን፡ ዓይኖቻችንም ተጨፍነው፡ ክርስቲያኖችም እየጸለዩ ባለበት፡ እጃችሁን ወደ ላይ ብታነሱና፡ እንዲህ ብትሉ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ አስበኝ። የ—የምትናገረው እያንዳንዱ ቃል ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ

እውነት እንደሆነ እምናለሁ። ሁላችንም በመንፈስ መሞላት አለብን፡ እኔ ግን፡ እስካሁን፡ አልተሞላሁም። የቤተ ክርስቲያን አባል ብቻ ነበርኩ” ብትሉ ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ። ወይም፡ ምናልባት እስከ ዛሬ አባል አልነበራችሁ፡ ይሆናል። ምናልባት ኃጢአተኛ ሆናችሁ፡ ክርስቶስን ፈጽሞ አልተቀበላችሁ ይሆናል። ወይም፡ የቤተክርስቲያን አባል ሆናችሁ፡ ዳግመኛ አልተወለዳችሁ ይሆናል። እጃችሁን ወደ ላይ አንሱና፡ እንዲህ በሉ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ በጸሎትህ፡ አስበኝ። ትክክለኛ መሆን እፈልጋለሁ።”

191 እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ አንተንም፡ አንተንም፡ አንተንም፡ አንተንም፥ ወንድሜ፡ አንተንም፥ እህቴ፡ አንቺንም፥ ወንድሜ፡ አንተንም፥ አንተንም፡ አንተንም፡ አንተንም፡ ወንድሜ፡ እህቴ፡ ሁላችሁንም እያችኋለሁ።

192 በግራዬ በኩል፡ ስንት ሰዎች አላችሁ? እጃችሁን አንሱና፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አስበኝ፡ ዳግመኛ መወለድ እፈልጋለሁ፡” በሉ።

193 አሁን፡ መንፈስ ቅዱስ እያናገራችሁ እንደሆነ፡ አስታውሱ። እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆንኩኝ፡ በዚህ መድረክ ላይ መቆሜ፡ እርግጠኛ እንደሆንኩ፡ መንፈስ ቅዱስ እዚህ ልቦችን እያናገረ እንደሆነ እርግጠኛ ነኝ። ወዳጆች ሆይ፡ ለእናንተ የተለየሁ ልመስል እችላለሁ፡ ነገር ግን እክራሪ አይደለሁም። የምናገረውን አውቃለሁ፥ ችግራችሁ ምን እንደሆነ፡ በሽታችሁ ምን እንደሆነ ካወቅኩና፡ እግዚአብሔር ስለ እናንተ ጸሎቴን ከሰማ… አሁኑኑ በዚህ ሕንፃ ውስጥ ከካንሰር፡ ከዕውርነት፡ ከደንቆሮነት፡ ከሽባነትና፡ ከሌሎችም በሽታዎች፡ የተፈወሱ ሰዎች ተቀምጠዋል፡ በዓለም ዙሪያ ያሉትን ስብሰባዎችም ተመልከቱ። ታዲያ ስለ እናንተስ? ታዲያ ስለዚያስ? ለዚያ ጸሎቴን ከሰማ፡ ስለ ነፍሳችሁ ሁኔታ ጸሎቴን አይሰማምን? ችግራቸው የት እንዳለ ከገለጠልኝ፡ አሁንስ፡ ችግራችሁ የት እንደሆነ አይገልጥልኝምን?

194 ስንቶቻችሁ እጃችሁን በማንሳት፡ እንዲህ፡ “ወንድም ብራንሃም ሆይ አስበኝ። በዚህ ሰዓት፡ እግዚአብሔር እንዲምረኝ መጠየቅ፡ እፈልጋለሁ” ትላላችሁ? እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ አንተንም፡ አንተንም፡ አንተንም፡ አንተንም። ኦህ፡ ማይ፡ በሕንፃው ሁሉ ውስጥ፡ በሁሉም ቦታ!

195 ራሳችሁን ዝቅ እንዳደረጋችሁ፡ እጃችሁን ያነሳችሁ ሰዎች፡ ትንሽ ተጨማሪ ጸጋ ይኑራችሁና፡ እንዲህ፡ ትላላችሁን፡ “ጌታ ሆይ፡ እጄን ለማንሳት የሚያስችል ጸጋ አግኝቻለሁ፡ እርሱ ሲጸልይ ደግሞ እንድቆም የሚበቃ ጸጋ ሰጠኝ። ጌታ ሆይ፡ ጎህ ሳይቀድ በፊት፡ ቢመጣ፡ ይህ ለእኔ ትክክለኛ መሆን እንደምፈልግ፡ ለአንተ የማሳየው ምልክቴ ነው። አንድ ቀን ከአንተ ጋር መገናኘት እፈልጋለሁ። የመጨረሻዋ ሳል ትመጣለችና የሞት ትራስ ላይም እተኛለሁና። ሐኪሙም የሚያደርገውን አጥቶ፥ ከአልጋዬ አጠገብ ይሄዳል። እንደዛ ከሆነ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ለነፍሴ ምህረትን አድርግላት። የሞት ቅዝቃዜ ያለው ጭጋግ ክፍሉን ሲሞላው፡ ያቺ የጽዮን ጥንታዊት መርከብ መጥታ፡ ትውሰደኝ። ጌታ ሆይ፡ እቆማለሁ። ብዙ ጸጋ ይጠይቃል፡ ነገር ግን የሆነ ነገር እያነሳሳኝ ነው። እየቆምኩ ነው።” እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ።

196 ሌላም ሰው ቆሞ፡ እንዲህ ይበል፡ “ጌታ ሆይ፡ እቆማለሁ” ይበል። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ፡ ወንድሜ።

ዝም ብላችሁ ቁሙ። በዚህ ጸሎት ለነፍሳችሁ መዳን፡ እንድትታሰቡ የምትፈልጉ ሁሉ፡ ትቆማላችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወጣት። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ጌታዬ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እህቴ፥ አንተንም፡ ወንድሜ።

197 አሁኑኑ ሌላ ሰው ይቁምና እንዲህ ይበል፡ “እነሆኝ። ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እኔ በአንተ ፊት ሳይሆን፡ በእግዚአብሔር ፊት ነው የቆምኩት። አንድ ነገር እንድቆም ነገረኝ፡ እኔም እየቆምኩ ነው” ይበል። ይህን ታደርጋላችሁ? በሁለት እግራችሁ ቁሙ። እግዚአብሔርን በዚህ ልክ እመኑት። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት።

198 ገና ብዙ አሉ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። በትክክል። አንዲት ምስኪን እናት ትንሹን ልጇን ታቅፋ፡ እንባ በዓይኖቿ ሞልቶ፡ ለመቆም እየሞከረች ነው። አትመጪም? እንደገና ቁሙ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት፡ በዕድሜ የገፉ አንዲት አረጋዊት እዚያ ቆመዋል፡ ከነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት እንዳለባት፡ አውቃለች። እግዚአብሔር ይባርክሽ። አሁን ቀጥሎ፡ “እቆማለሁ” የሚል ማን አለ?

ለጸሎቱ ዝም ብላችሁ ቁሙ።

199 ሌላ ሰው አለ? ሌላ መቆም የሚፈልግ ሰው እንዳለ ይሰማኛል። ምናልባት ጥቂት ለመቅረብ ትፈልጉ ይሆናል። ከእንግዲህ አታዘግዩት። ዝም ብላችሁ ቁሙ። ይህን ታደርጋላችሁ? ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የምትፈልጉ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። በትክክል። የሆነ ሰው... እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። አዎ፡ ጌታዬ።

200 ቢያንስ ሦስት ተጨማሪ ሰዎች፡ ቀጥታ እያየኋቸው ያለሁት፡ መቆም ያለባቸው አሉ፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር መልአክ እዚያ ቆሟል። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። በትክክል። አሁን፡ መልካም፡ ወንድሜ፡ አንተስ? መልካም። የእግዚአብሔር መልአክ፡ ቆሞአል፡ አውቃለሁ። እየዋለሁ፡ አሁን አንድ ሰው መቆም እንዳለበት አውቃለሁ። ለጥቂት ደቂቃ እጠብቃለሁ። እግዚአብሔር... እርሱ ልባችሁን እያነሳሳው እንደሆነ ታውቃላችሁ። እርሱ እዚያ ቆሟል፡ ወዳጄ። እንድትቆም እየነገረህ ያለው እርሱ ነው። አታደርገውም? አሁኑኑ ቆመህ፡ እርሱን ተቀበል። መልካም።

201 አሁን እርግጠኛ ናችሁ? እግዚአብሔር ዛሬ ምሽት፡ በዚህ ስብሰባ ላይ ቢጠራችሁ፥ ይህ ስብከት፡ ይህ ግብዣ፡ ከሞታችሁ በኋላ እዚያ ማዶ ያገኛችኋል። ታዲያ ስለ እሱ ምን አደረጋችሁ? እርግጠኛ ካልሆናችሁ፡ ለመቀበልና፡ በብርሃን ለመመላለስ፡ እንደምትፈልጉ፡ ያይ ዘንድ አሁን ቁሙ።

202 አሁን፡ ቸሩ የሰማይ አባታችን ሆይ፡ እነዚህ ውድ ልጆችህ፡ በልባቸው ትሁት የሆኑት፡ ዛሬ ምሽት ቃሉ በልባቸው ውሰጥ ወደቀ። “እምነት ከመስማት ነው፡ መስማትም ከቃሉ ነው።” አንተም ሰምተሃል። አንተም ልባቸውን አራራኸው፡ ብዙዎች ቆመዋል፡ ወንዶችና ሴቶች፡ ወንድና ሴት ልጆች፡ አንተን እንደ ውድ አዳኛቸውና መሪያቸው አድርገው እየመሰከሩ ነው።

203 ዛሬ ምሽት እዚህ ያለው፡ የእግዚአብሔር መልአክ፡ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ይምራቸው። አሁኑኑ በልባቸው፡ ወደ ቀራንዮ ይመሩ፡ ኢየሱስን እንደ

አዳኛቸው ይቀበሉ። መንፈስ ቅዱስም፡ በክርስቶስ ደም በኩል፡ በነፍሳቸው ላይ ይውረድ፡ ግድየለሽነትንም ሁሉ ያስወግድ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም ይሙላቸው። ይህ በሕይወታቸው ታላቁ ምሽት ይሁን። ዛሬ ምሽት እንተን እየተቀበሉህ ነውና፡ እንደዚያ እንደሚሆን እናውቃለን። ጌታ ሆይ፡ አሁን፡ ይሁንልን። ዛሬ ምሽት፡ ከዚህ ወደቤታቸው ሲሄዱ፡ ደስተኛ ሆነውና እየተደሰቱ፡ በፍጹም ልባቸው፡ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ቤታቸው ይሂዱ። ይህን በረከት በክርስቶስ ኢየሱስ ስም እጸልያለሁ።

አሁን ስትቀመጡ ጌታ ይባርካችሁ።

204 አሁን ልጠይቃችሁ፡ የቆማችሁት እያንዳንዳችሁ፡ ቆማችሁ ሳለ አንድ ነገር እንደተሰማችሁ ካወቃችሁ፡ እጃችሁን አንሱ። የሆነ ነገር እንደሆነ ካወቃችሁ፡ ዝም ብላችሁ እጃችሁን አንሱ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። በትክክል። ወዳጆች ሆይ፡ መሆን አለበት። መሆን አለበት። አሁኑ እዚህ፡ ቆሜ፡ የምናገረውን ያንኑ መልአክ፡ በዚህ ሕንፃ ውስጥ ሲያልፍ አየሁት፥ ያው የጌታ መልአክ፡ የእሳቱ ዓምድ። ባለፉት አምስት ወይም አሥር ደቂቃዎች ውስጥ፡ በዚያ ምሪት ስር እየሰበክሁ ነበር። ይሰማኛል፡ በዚህ ሕንፃ ውስጥ ሲንቀሳቀስ እየዋለሁ። አሁን፡ ተረት የምነግራችሁ ሊመስላችሁ ይችላል፡ ግን እውነቱ ይህ ነው።

205 አሁን፡ የጸሎት ሰልፍ እንኳ የምጠራ አይመስለኝም። እውነቱን እንደነገርኳችሁ እግዚአብሔር በምልክቶችና በድንቆች ያረጋግጥልኛ ዘንድ፡ እዚሁ ቆሜ፡ የምጠይቅ ይመስለኛል፡ በትክክል።

206 የከእናንተ መካከል መፈወስ የሚፈልጉ፡ ታማሚዎች ስንት ናችሁ? ያላችሁበት ሆናችሁ፡ እጃችሁን አንሱ። ዝም ብላችሁ እጃችሁን አንሱና፡ "እቀበላለሁ፡" በሉ። እሺ።

207 እንድትመለከቱ፡ በሕይወት እንድትኖሩና፡ እንድታምኑ እፈልጋለሁ። ከዚህ ጉባኤ መካከል የሆነ ሰው፡ **እዚህ** አካባቢ፡ እዚህም አካባቢ፡ ዝም ብለህ ተመልከትና፡ እንዲህ በል፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ... "

208 እንደዚህ። መጀመሪያ የመሠዊያ ጥሪ ያደረግሁበት ምክንያት፡ በእርሱ ዘንድ ሞገስ ማግኘት ስላለብን እንደሆነ፡ አምናለሁ። ይህ ለእኔ አዲስ ነገር ነው። መጀመሪያ በእርሱ ዘንድ፡ ሞገስ ማግኘት አለብኝ። ከዚያም ሞገስን ካገኘሁና፡ መልካም ነገርን ካደረግሁ... የተወሰናችሁ፡ ወይም ሁለት ያህል ነፍሳት አሁን ወደ እርሱ መጥታችኋል። እውነት፡ በእውነት...

209 አሁን፡ ወደ ክርስቶስ የመጣችሁ እያንዳንዳችሁ፡ ከዚያም፡ ጥሩ በመንፈስ-ቅዱስ-የተሞላች ቤተ ክርስቲያን ፈልጉና ሂዱ። እዚያም እስክታገኙት ድረስ የእርሱን ጥምቀት ተመኙ፥ ዝም ብላችሁ ሂዱ፡ በየምሽቱ፡ በየቀኑ፡ መጸለይን ቀጥሉ። ስትመለከቱም...

210 አሁን እናንተ የታመማችሁ ሰዎች፡ እውነቱን ነግሬያችሁ ከሆነ፡ እውነት መሆኑን እግዚአብሔር ይመሰክራል። በትክክል። እርሱ ብቻ ነው ሊያደርገው የሚችለው። በፍጹም ልባችሁ ብትጸልዩና ብታምኑ፡ እግዚአብሔር እንዲታወቅ ያደርገዋል። ዝም ብላችሁ ተመልከቱና፡ እንዲህ በሉ...

211 ከሰምንት ዓመት በፊት፡ በግሪን ሚል፡ ኢንዲያና፡ ከሕፃንነቴ ጀምሮ፡ እየተከተለኝ፡ ራእዮችን ሲያሳየኝ የቆየው፡ ያ የእግዚአብሔር መልአክ ሲያገኘኝና፡ ወደ እርሱ ሰቀርብ እንዲህ አለኝ፡ "ቅን ከሆንክና፡ ሰዎቹ እንዲያምኑህ ካደረግሃቸው፡ ጸሎትህን ሊቋቋም የሚችል ምንም ነገር አይኖርም" አለኝ።

212 አሁን፡ ያን ጊዜ እንዳደረገው ሁሉ አሁንም ለእናንተ ያንኑ ማድረግ ይችላል። እርሱ ከሙታን ተነሥቷል። እሱም... ይኸው ሕዝቡም በፊቱ አለ። በእያንዳንዳችሁ ላይ ምን እንዳለ፡ ምን እንዳደረጋችሁ፡ ችግራችሁ ምን እንደሆነና፡ ሰለ ሁሉም ነገር ያውቃል። ይህን ታምናላችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አአታዒ።] እንግዲያውስ በፍጹም ልባችሁ እመኑ።

213 እዚህ አንድ ወጣት ተቀምጦ፡ አምኖ፡ እምነት ለማግኘት፡ ሲጣጣር አያለሁ። እግዚአብሔር ምን እንደሆንክ እንደሚያሳውቀኝ ታምናለህ? ታምናለህ? ካሳወቀኝስ፡ ፈውስህን ትቀበላለህ? የልብ ህመም አለብህ። ልክ አይደለም? አሁን ከእሱ እንደዳንክ ብነግርህስ? ታምናለህ? ለአንድ አፍታ ቁም እስቲ። የልብ መረበሸና፡ የልብ ትርታ አለብህ። ይህ ለተወሰነ ጊዜ አስጨንቆሃል። ብቸኛው ጊዜ... እንዲሁም፡ ሰትተኛ ያፍንሃም፡ ልብህም ወዲያና ወዲህ ይመታል፡ ይርገበገባል። ልክ ነው? ምክንያቱም፡ ይህም በደም ሥሮችህ በኩል ወደ ላይ በመውጣት በሆድህ ላይ፡ የምግብ አለመፈጨት ችግርን ይፈጥራል። ይህ እውነት አይደለምን? ከእንግዲህ በዚህ አትሰቃይም። አሁን ያለህን እምነት ብቻ ያዝ፥ ወደ ቤትህ ሄደህ መዳን ትችላለህ።

214 አእምህን እያነበብኩ አይደለም። ለአንተ ፈጽሞ እንግዳ ነኝ። አንተ ዝም ብለህ እዚያ የተቀመጥክ ሰው ነህ። ልክ ነው? በሕይወቴ አይቼህ አላውቅም፡ ሰለ አንተም ምንም አላውቅም ነበር። ይህ እውነት አይደለምን? ጌታ እዚህ እንዳለ እመን!

215 እውነቱን ለመናገር፡ አንተ ወጣት፡ አንድ ነገር ልጠይቅህ፡ ይህ እውነት መሆኑን ወይም አለመሆኑን ተመልከት። ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት፡ ማውራት ሰጀምር፡ በድንገት አንድ እንግዳ ነገር ተሰማህ ሰለ "መርዙ ከነዳፊው እንደወጣ" ሰናገር። አይደለም እንዴ? እዚያ ተቀምጠህ-ሳለ፡ አንድ እንግዳ ሰሜት አልተሰማህም? ልክ አይደለም ወይ? በዚያውም ቅጽበት ወደ እኔ አላየህም፡ ዓይኖቻችንስ በዚያው ቅጽበት አልተጋጩም? ልክ በዚያን ጊዜ ነው፡ ከልብ ህመምህ፡ የተፈወሰከው። አሜን። በትክክል። እርሱ እዚህ አለ።

216 ወዳጆች ሆይ፡ አእምሯችሁን እያነበብኩ አይደለም። እውነት ብቻ ተናግሬአለሁ፡ እግዚአብሔርም እውነት መሆኑን ያረጋግጣል ።

217 ከእርሱ አጠገብ የተቀመጥከው፡ ምን ታስባለህ? ታምናለህ? የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩ ታምናለህ? እግዚአብሔር እንዲህ ቢያደርግ ታምነዋለህ... እዚህ ፊት ለፊት፡ የተቀመጥከው፡ እኔን የከበበኝ መንፈስ፡ ወደ አንተም ሰለደረሰ ነው፡ እንዲህ ደጋግሜ የማናግርህ። ነገር ግን ከመንፈስህ ጋር ብገናኝ፡ እግዚአብሔር ችግርህ ምን እንደሆነ ይገልጣል ብለህ፡ ታምናለህ? ፈውስህን ትቀበላለህ? የስኳር ታማሚ ነህ። ልክ ነው? እውነት ከሆነ እጅህን አንሳ። በእግርህ ቁም። አሁን ፈውስህን ትቀበላለህ? ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ይፈውስህ። እግዚአብሔር ይባርክህ።

218 እምነት ይኑራችሁ። **እዚህ** ያለ አንድ ሰው እምን። በፍጹም ልባችሁ፡ እምነት ይኑራችሁ።

219 እዚያ ሰማያዊ ልብስ የለበሰ ወጣት ተቀምጦ አያለሁ። ብርሃኑ ልክ ከእርሱ በላይ ቆሟል። የቆዳ በሽታ አለብህ፡ አይደል፡ አንተ ወጣት? ልክ አይደለም? በእግርህ ቁም። ኦህ፡ አየሁ፡ ከዚህ የልዑካን ቡድን ጋር ነህ። ልክ ነው? እንግዲያውስ ደህና ሆነህ ወደ ቤት መሄድ ትፈልጋለህ? እጅህን አንሳና እንዲህ በል፡ “ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አሁን የእግዚአብሔር መልአክ እየመራ እንደሆነ አምናለሁ። እንደተፈወስኩም አምናለሁ።”

220 ከእርሱ አጠገብ ያለኸው ሰው፡ አንተስ ምን ታስባለህ፡ አንተስ፡ ታምናለህ? እንድመለከትህ፡ ለአንድ አፍታ ቁም። እኔ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆንኩ በፍጹም ልብህ ታምናለህ? ከዛ የልብ ህመምህ መፈወስ ትፈልጋለህ? የነበረብህ እሱ ነበር፡ አይደል? “**የነበረብህ**” ነው፡ ያልኩት። አሁን የለብህም። አንተም፡ ወደ ቤትህ መሄድ ትችላለህ።

221 ከእርሱ አጠገብ ያለኸው ሰው፡ አንተስ ስለዚህ ምን ታስባለህ፡ ጌታዬ? በፍጹም ልብህ ታምናለህ? የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩ ታምናለህ? በእግርህ ቁም። አሁን በፍጹም ልብህ ታምናለህ? የነርቭ መረበሽ ነበረብህ። ልክ አይደለም? አየህ? ልክ ነው? እጅህን አንሳ። አሁን ደህና ሆነህ ወደ ቤትህ መሄድ ትችላለህ። ኢየሱስ ክርስቶስ ፈውሶሃል።

222 በዚያው ረድፍ ላይ፡ ቀጥሎ ያለው ሰው፡ ቁም፡ አንተስ በፍጹም ልብህ ታምናለህ? በእግርህ ቁም። እኔ የእግዚአብሔር ነቢይና፡ አገልጋዩ እንደሆንኩ ታምናለህ? ችግርህ ምን እንደሆነ እርሱ ቢነግረኝ፡ ፈውስህን እንደምትቀበል ታምናለህ? ሕመሙ ጉሮሮህ ውስጥ ነው። ልክ ነው? በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ወደ ቤትህ ሂድና ተፈወስ።

223 በዚህ ሕንፃ ውስጥ፡ መፈወስ የሚፈልግ ሌላ ማንኛውም ሰው፡ ተነስቶ መፈወስ ይችላል። እኔን እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ፡ አምናችሁኝ ከሆነ፡ በእግሮቻችሁ ቁሙ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። የሴቶች ሕመም፡ ካንሰር፡ እየሄደ ነው። እግዚአብሔር ይባረክ! እያንዳንዳችሁ፡ እጆቻችሁን ወደ እግዚአብሔር አንሱ።

224 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ አሁን በዚህ ሕንፃ ውስጥ ያለውን እያንዳንዱን በሽታ እገስጻለሁ፡ እያንዳንዱንም ክፉ መንፈስ አስወጣለሁ፡ አሁኑኑ መንፈስ ቅዱስ ሰፍራውን ይረከብና እያንዳንዱን ሰው ይፈውስ።

225 እርስ በርሳችሁ እጆቻችሁን ተጫጫኑና፡ በሁሉም ቦታ፡ “ጌታ ይመስገን፡” በሉ። ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ፡ እያንዳንዳችሁን፡ ይፈውስ ዘንድ፡ የእግዚአብሔር በግ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ አለና።

54-0329 ቤዛነት በኃይል
ቸርች ኦፍ ዚ ኦፕን ዶር
ሎይስቪል፣ ኬንታኪ ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org